# የአማርኛ ግጥሞች

## ሀ

ሀረር ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉ ሸዋ
ልታንከራትተኝ አሸዋ ለአሸዋ
ሸዋ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ መንዝ
ከኛ ከጠንቀኞች ጦር ልታማዝዝ
መንዝ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ ወሎ
አይኗ የሚመስለው የብረት አለሎ
ወሎ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ ደሴ
ሳዱላዋን ገጥማ ሆናለች ፈሰሴ
ደሴ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ ጎንደር
ይመልከተው እንጂ አምላክ ፈጣሪ እግዜር
ጎንደር ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉ ትግሬ
እከተላታለሁ በለመደው እግሬ
ትግሬ ላይ ባስጠይቅ ናት አሉኝ መቀሌ
እከተላታለሁ እኔው እንደ አመሌ
መቀሌ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ የጁ
ይዟታል ወረሴ በማሩም በጠጁ
የጁ ላይ ባስጠይቅ ናት አሉኝ ዉርጌሳ
አገሬን ለቀኩኝ በሷ የተነሳ
ውርጌሳ ባስጠይቅ ገባች አሉ አምባሰል
የዳገቱ ክፋት ጠቆርኩ እንደ ከሰል
አምባሰል ባስጠይቅ ነች አሉኝ አልብኮ
ከመንገሻ አቦየ ልታጣላኝ እኮ
አልብኮ ባስጠይቅ ናት አሉኝ ርቄ
እከተላታለሁ ንብረቴን ለቅቄ
ርቄ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ ቦሩ
እናቲቱ ናቸው ይህን የሚሰሩ
ቦሩ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉ ቃሉ
እንኳን ሂዳላቸው ደርሰው ይቃማሉ
ቃሉ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ አውሳ
እያደር ገነነች እንኳን ልትረሳ
አውሳ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ አሰብ
ያቺ ልጅ ተገኘች ጎረቤት ተሰብሰብ
አሰብ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ ሰማይ

የት እመለሳለሁ መድረሻዋን ሳላይ
ሰማይ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉኝ ጎጃም
እንግዲህስ በቃኝ ነገር አላንዛዛም
ጎጃሞች ካገኟት መቼ ይለቋታል
በማርሩም በጠጁም እዛው ያስምዷታል።

ሀረር ድሬ ደዋ ጂቡቲ ድንበር
እኔና አንቺ ሆነን ሶስተኛው እግዜር
ምን ብለሽኝ ነበር ምን ብየሽ ነበር?

ሀብት ያለው ገባና ሃብት የሌለኝ ቆሜ
አጥርሽን ጨረስኩት ቆርጥሜ ቆርጥሜ

ሁለቱንም አይኔን ዳመና ጋለበት
ብዙ ነገር አይቷል ይጥፋ ምናለበት

ሁልጊዜ ጎፈሬ ተበጥሮ ኑሮ
ላኪልኝ መቀሱን ቁርጥ ነው ዘንድሮ

ሂዱ ሂዱ ይላል ብረሩ ብረሩ
አንድ የሚወዱት ሰው ሲጠፉ ካገሩ

ሂጂልኝ ወድያልኝ ፍቅርሽ መላም የለው
ጊዜ ለሰጠው ሰው ታደያለሽ ምነው?

ሃሜተኛም ይማ ለዋሽም ይለውስ
እጅዋን በጄ ይዤ እጨሃለሁ ለንጉስ

ሃምሌ ነሃሴ መጣ ሁለት ወር ክረምት
ለልቤ ማረፊያ ቤት ሳልሰራለት

ሃምሌ ነሃሴ መጣ ስሩ ደነደነ
የወር ቀለብ የለኝ ቤቴ አልተከደነ

ሃምሌ ድንጋይ ይዟል ሰው ሲገልላችሁ
ነሃሴ ጦር መዟል ሰው ሲገልላችሁ
አትገላግሉም ወይ ያላችሁ ያላችሁ?

ህመሜ በሰው ፊት እንዳታዋርደኝ
እኔኑ ብቻየን ጉስም ጉስም አርገኝ

ሆዴ እንደመንደዱ ፍምም አልወረደው
እህል እየበላ ውሃ እያበረደው

ሆዴ እየነደደ ቢሸተው አንጀቴ
ስጋ ጠብሷል ብሎ አማኝ ጎረቤቴ

ሆዴ እየነደደ ጥርሴ እየመለሰው
አሁን በጎ አዳሪ እመስላለሁ ለሰው

ሆዴን ባርባር አለው ወልዶ እንደቀበረ
ተዋዶ መለየት በኔ አልተጀመረ

# ለ

ለማማት ቢሄዱ የሚያስኮንን ቢሆን
ለነፍሱስ የሚያድረው የሚያርፈው ማን ይሆን?

ለበለቡት አሉ ያለሸበትን
ሰው እጠይቃለሁ አርረሽ እንደሆን

ለነገረ ሰሪው ለሃሜተኛው ብየ
ራቴ ቂጣ ነው ሳላቦካ ውየ

ለአንበሳ ተድረሽ ነብር ከጅሎሻል
አወይ የአንቺ ነገር ዝንጀሮ ያምርሻል

ለአንተ ይብላኝ እንጂ ለእኔማ ተመቸኝ
እወደው ነበረ ማለት አይሰለቸኝ

ለአንቺ ይመስልሻል ብቻየን ሄጃለሁ
ዘወር በይ ያገር ልጅ ተከትየሻለሁ

ለአንቺ ይብላኝ እንጂ ለወዳጅ አባይ
እኔማ የእድሌን አጣዋለሁ ወይ?

ለአንች ይብላኝ እንጂ ምስጋና ላጣሽው
ልቤማ ጠገበሸ በልሜ እየታየሽው


3

ለአንቺ ይብላኝ እንጂ ቃልሽ ለፈረሰው
መቼ ወዳጅ ያጣል ቆሞ ከሄደ ሰው

ለከተማው ዳኛ ነግሬ ለሹሙ
ይፋ አወጣሻለሁ ካልቀረልኝ ስሙ

ለከንቱ መኝታ እየተጋደምሁ
ቅር እያለው ሆዴን ኩነኔ ገባሁ

ለዛች ለአገራችን ውለዱላት መንታ
አተላው ተቀምጦ ጀግና ሰው ተመታ

ለየካ ሚካኤል አትሳይም ወይ
ለቁልቢ ገብርኤል አትሳይም ወይ
አክሱም ፅዮን ማርያም አትሳይም ወይ
ጉለሌ ሩፋኤል አትሳይም ወይ
ወሎ ግሸን ማርያም አትሳይም ወይ
ከኔ መለየቱን ወደሽዋል ወይ?
ካንተ መለየቱን ምን እወደዋለሁ
ለአርባ አራቱም ታቦት ተስየልሃለሁ

ለገሃር ታምሜ አዋሽ ላይ ሳገግም
በሽታየ ጠና ድሬደዋ ላዝግም

ሌባ የሌባ ልጅ መስረቅ የለመደች
በጅዋ ባይሆንላት በአይኗ ሰርቃኝ ሄደች

ልቤማ ልባሙ ሄደ ገሰገሰ
አይኔ በስንፍናው ቀረ እያለቀሰ

ልቤ ቆላ ወርዶ ይዞ መጣ ንዳድ
ይበል ያንቀጥቅጠው ይህ መከራ ወዳድ

ልቤ ቆላ ወርዶ ጥጥ ይፈለቅቃል
ከወደዱ ወዲያ ምን ያሞላቅቃል

ልቤን መልስልኝ ብለሽ የላክሽብኝ
አንቺው ጋር ይቀመጥ እኔም ያንቺ አለብኝ

ልቤን መልሽልኝ ልብሽ ይበቃሻል
በልብ የከበሩ እነማን አይተሻል?

ልቤን ደቁሱና ሳኩልኝ ዱቄቱን
ወትሮስ ያስሰፍራው ማን ግባ አለው ጥንቱን

ልቤ ኩታ አሰፋ ለብሶ ሳይጨርሰው
ወትሮም ልማዴ ነው አሳልፎ ለሰው

ልቤ ዞሮ ዞሮ እስከ አለም ዳርቻ
አውርቶ እሚመጣው ያንቺን ዝና ብቻ

ልቤ ገሰገሰ በእኩለ ለሊት
አልመታሁት እንኳን አልተቆጣሁት

ልቤ ጫካ ነበር ዝሆን የማይጥሰው
ተመነቃቀረ ዘንድሮ በአንድ ሰው

ልጅቱ ገዳም ነች አይገባም ሴት ሴቱ
ይቀበሩባታል ወንዶች እየሞቱ

ልጠባው መሰለኝ በጥብጨ አፈሩን
እኔም እንደ ወሎች አምር እንደሆን

ልጠባው በጥብጨ የወሎን አፈር
እኔም እንደነሱ ምናልባት በአምር

## መ

መሄዱንስ ሂጂ ለማን አደራ አልሽኝ
በፍቅርሽ ተይዤ ስርድ እያየሽኝ

መሂድሽ ነው አሉ መሂድሽ ይወራል
እንግዲህማ አይኔ ማን አይቶ ይኖራል

መለየት መለየት መለየት ክፉ ሰው
እንደ አባ ጨጓሬ የሚኮሰኩሰው

መለያየት ክፉ በቁም መቀበር
በትዝታሽ ገርፎ ያስጮኸኝ ጀመር


5

መላ ያጣ ነገር ቅጡ የተዛባ
ሲዞር ሲዞር ከርሞ ልቤ ገደል ገባ

መልኬ ብቻ በቃኝ የምትል እንደሆን
እንኳንስ ለባሏ ለእናቷም አትሆን

መልካም ጠባይ ያላት የወለዱ እንደሆን
ታመጣለች አማች ብረት መዝጊያ እሚሆን

መስታወት ፊት እንጂ አያሳይም አገር
እግዜር አደራህን የዛችን ልጅ ነገር

መስኮቱ ተከፍቶ ቢታየኝ ደረቷ
እኔስ መስሎኝ ነበር ተቃጠለ ቤቷ

መሸ በሩን ዝጉት ከቀረ ልማዴ
ተከፍቶ ማደሩን አይወደውም ሆዴ

መቀመጥሽ ነው ወይ ትዳሬ ብለሽ
ልቤን እንደ ፋኖስ ከራስጌሽ ሰቅለሽ

መተማ ድል ሆኖ አድዋ ሲበረበር
እናቱ ወልደውት እኔ አርግዤው ነበር

መተው እተዋለሁ በዋስ ተፈጥሜ
እሷን ከልክሉልኝ እንዳትመጣ በልሜ

መቼ ትመጫለሽ አንቺ መንገደኛ
እየራቀ ሄደ የኛ መገናኛ

መንደርተኛው ሁሉ እሳት ጫሪ ነው
የአንቺን ገል አደራ ሰው እንዳይነካው

መንገድ አይንህ ይፍሰስ አይባልም ደርሶ
የወሰደውን ሰው ያመጣል መልሶ

መኝታው ጠባብ ነው ሰውም አይጨም-ር
ይሁን እሷ መጥታ ሲጠበኝ ልደር

መገን እኔና አንቺ ችጋር የምናልቀው
ሸምተን አንበላ አገሩን እናውቀው

መጣሁም አንድ ነው ቀረሁም አንድ ነው
እንዲያው ከመሃል ላይ መዋለል ምንድን ነው?

ማሲንቆም አልሻ የፈረስ ጭራ ነው
ዋሸንትም አልፈልግ ወንዝ ዳር በቀል ነው
ከበሮም ይቅርብኝ የበሬ ቆዳ ነው
አምጡልኝ ክራሬን አንጀትን በአንጀት ነው

ማሲንቆና ክራር ማማሩ በኛ እጅ
እየቃኙ ለሰው ለመደብን እንጅ

ማሲንቆና ክራር እያለልኝ በእጄ
ያብከነክነኛል በገና ወድጄ

ማን አባቱ ያዘኛል ምን የኀበረበት
በገዛ ትዳሬ ውሃ ብደፋበት

ምር አዘነ ሆዴ ቁረንጮ ታጠቀ
ወዳጅ ምን ያደርጋል አገሩ ከራቀ

ምሳር ላወቀበት ደን ይመነጥራል
አትቀደም ያለው በአይን ይጠረጥራል

ምሳየንም በላሁ አመሰገንኳችሁ
ራቴንም በላሁ አመሰገንኳችሁ
ይኸ ብቻ ማደር ትኮነናላችሁ

ምነዋ ደረቴን ምነው የጡቴን ስር
የዋለ ያደረ ጠብ ያለን ይመስል

ምነው ባላየሁሽ ባልተገናኘን
ርሃብ ሊገለኝ ነው ያንቺ ሰቀቀን

ምነው ባደረገኝ የደጁን አበባ
እጥፍ ቅጥፍ አርጎ ይዞኝ እንዲገባ

*ምነው አምና በሞትኩ እንዲያ እንዳማረብኝ*
*በኩታ ላይ ኬሻ ሳይደረብብኝ*

*ምነው ከሃገር ልጅ አብረው ቢሰደዱ*
*ቢያገኝም ያበላል ቢያጣም ያዝናል ሆዱ*

*ምነው ከሳህ ጠቆርክ ይለኛል ባላገር*
*የሆዴን አውጥቼ ለስንቱ ልናገር*

*ምነው ከሳሽ ጠቆርሽ ሆነ ጥያቄያቸው*
*ሰው አለ በሆዴ እንዴት ላሳያቸው?*

*ምነው ዛሬ በሞትኩ ምነው ነገ በሞትኩ*
*አይንሽን አይኔ አይቶት አፍሽን አፌ ስሞት*

*ምኑ ነው መኝታ ስንዝር እየራቁ*
*ከሰው ጋር ተኝቶ ሰው እየናፈቁ*

*ምናልባት ሰው ሆነሽ ብታሰስጠይቂኝ*
*ጦሳ ጋራ በታች መሃል ደሴ ነኝ*

*ምን ሃብታም ብትሆኝ ሃብታም ቢወልድሽ*
*አገሩን ግዢ እንጂ ልቤን ምን ገዶሽ*

*ምንስ እኔ ብሆን ጊዜ ቢጥለኝ*
*አንበሳው ተቀምጦ ውሻ ነከሰኝ*

*ምን ብለሽኝ ነበር ምን ብየሽ ነበር*
*ወይ አጅሬ ምላስ ወድቆ አይሰበር*

*ምንኛ ደስ ይላል ከእኩያ ጨዋታ*
*እሷ የእኔ እመቤት እኔ የሷ ጌታ*

*ምንኛ ደግ ነው ስሜነኛ መሆን*
*ከወገራ አልፌ አገኛት እንደሆን*

ምንኛ ደግ ነው ውሃ መሰለል
አያል ሰው ወሰደ ዘንድሮ አምባሰል


8

ምን አንጀት ቢረዝም ከመጫኛ ቢጠብቅ
ከቦታው ይጠፋል ሲበጠስ ሲቆረጥ

ምን ወንዝ አበቀለሽ እንዴት አይነት ቦታ
የተጫወትሽው ሰው ያብዳል ማታ ማታ

ምን ያለው አሞራ ከግንድ ይሟገታል
ከሚወዱት ጋራ ማን ሲኖር አይቶታል

ምን ያሉ ቄስ ናቸው ተዝካር የለመዱ
አስታርቁኝ ብላቸው ፍታት ብለው ሄዱ

ምን ያስለፈልፋል የቆጥ የማገሩን
የመጣህበትን ስናውቀው ነገሩን

ምን ያደርግልኛል ያልሆነ ሳሙና
የማትቀየረው ትምጣ የኔ ገላ

ምን ያጣላችኋል በመሬት ጉዳይ
አሁን ዘር ሲጠፋ ይቀር የለም ወይ?

ምንድን ነው እየየ እንደ መንፌቅ ልጅ
ህመሜን ሰው ሰምቶት እሞታለሁ እንጂ

ምንጣፏ ስጋጃ ትራሷ  ዳዊት
ገብርኤል አሳላፊ ሚካኤል ወጥ ቤት
ከድንጋይ ላይ ውሃ የፈለቀላት
ከባህር ላይ እሳት የነደደላት
ንጉሱም ይላሉ አምጡና እንያት
አቡኑም ይላሉ አምጡ እንባርካት
እጥር ምጥን ያለች የልጅ እመቤት
ተጨንቆ ተጠቦ አምላክ የሰራት
የወሎ ሳዱላ መኳንንት የአጫት
አትለማም አትሰማም እኔ እዚህ ስሞት
ጨዋታው ቀርቶብኝ አይኗን ባየኋት

ሞትና መለየት ምን አንድ አደረገው
ያው ሞቱ ይሻላል ቁርጡ የታወቀው

ሞት ይሙት ይላሉ ሞት ቢሞት አልወድም
አፈሩ ድንጋዩ ከሰው ፊት አይከብድም

## ረ

ራሴን በዱላ ሽንጤን በጎራዴ
አገጩን በቡጢ ሳንጃውን በሆዴ
ደረቴን በጥይት ደም በደም ሳላይ
ያቺን ልጅ በዋዛ መልቀቅ አለ ወይ?

ራበኝ መሰለኝ ጎኔን ጎኔ ወጋው
አንቺ አለሽኝ ብየ ሳልሸምት በበጋው

ራበኝ አልራበኝ ሆዴን ማን ጠየቀው
አንድ እሱ ነበረ ጉዳቴን የሚያውቀው

ራበኝ እናቴ ውሃ ጠማኝ እቴ
ጉዳቴን ማን ያውቃል ካለመቀነቴ

ራብ ራብ አለኝ ኧረ እኔስ አላቅም
የተሰረቀ እህል ምን ቢሉት አይጠቅም

ርሃብ በእህል ያልፋል ጊዜ በተረት
ጭንቅ በሳቅ ያልፋል ፍቅር በወረት
ምንም ብንለፋ ምንም ብንታክት
ሳናልፈው አንቀርም የጭንቁን ወራት
አለመሞት መልካም በእድሜ መሰንበት
በአንድ ላይ ያታያል ወዳጅም ጠላት

ርግብና ዋኔ አብረው ዘመቱና
እርግብ ደህና ገባች ዋኔን ገደሉና

ሮማን ከንፈርሽ የሸንኮራ እሸት ነው
ቢበሉት ያጠግባል ቢጠጡትም ማር ነው

## ሰ


10

ሰማይ ሙሉ ኮከብ አድማቂው ጨረቃ
የታማንበትን ተይ በልተን እናብቃ

ሰማይ ምድር አልፎ ሁለታችን ቀርተን
ኋላ ሰው ይፈጠር ተጫውተን ተጫውተን

ሰማይን የሚያክል ብራና ተፍቆ
አባይን የሚያክል ቀለም ተበጥብጦ
ፍቅርሽና ፍቅሬ ባንድ ላይ ተፅፎ
ሳንጠጣው ቀረን ቀዳዳው አፍስሶ

ሰማይ ደም መሰለ ሲነጋ ለሊቱ
ጭንቅ ነው ጥብ ነው ካንቺ መለየቱ

ሰረገላም ባይኖር ባይሳፈር ጋሪ
መንገድ አይታክተው ለወሬ ነጋሪ

ሰቆጣም ሰቆጣ ቃሉም ቃሉ ነው
እንዴት የጁን ትቶ ይባክናል ሰው

ሰተት ብለሽ ግቢ በሩ ክፍት ነው
ምን ያስጨንቀዋል የመንደሩን ሰው
የመጣውን እዳ እኔ ልችለው

ሰኔ አጉረመረመ ሃምሌን ተንተርሶ
የወሰደሽ ንፋስ ያምጣልኝ መልሶ

ሰኞ ማክሰኞ አልፎ ቅዳሜ ብትለኝ
ሃሙስን አላልፍም አርብ አመት መሰለኝ

ሰው ሁሉ ተኝቶ እንቅልፉን ይልፋል
ልቤ ሰው ቤት ገብቶ መውጫ አጥቶ ይለፋል

ሰው ሁሉ በሽታው ራስ ወገቡን ነው
የኔስ በሽታየ ባቴ ነው ባቴ ነው

ሰው ማለት ሰው ማለት ሰው ማለት ሰው ማለት
ሰው የሚሆን ሰው ነው ውሉ የጠፋ ለት

ሰውማ ሰውማ ሰውማ መች ጠፋ

እምቢ አለኝ ሚዛኑ ወዳንቺ እየደፋ

ሰው ብልክ አይሰላ ብመጣ አላገኝሽ
እንደ እየሩሳሌም አድራለሁ ስመኝሽ

ሰው ገዳይ ነሽ አሉ ስሰማ ዝናሽን
ካሁኑ ፈራሁሽ እኔን አደራሽን

ሰዎቹ ይሉናል አበ ልጆች ናቸው
ነገሩ ወዲህ ነው የኔና የሳቸው

ሰይፍና ጎራዴ ትታጠቃላችሁ
አንጀት ቆርጦ እሚጥል ቅናት አለላችሁ

ሱሪየን አውልቄ ተንተርሸዋለሁ
ቀን የመጣ ለታ እታጠቀዋለሁ

ሲሆን አይሸበር አለዚያም ግድ የለኝ
እናቴም ልጅ አላት እኔም ወንድም አለኝ

ሲታመሙ ታሞ ሲሞቱ ካልሞቱ
በምን ያስታውቃል ሰው ወዳጅነቱ

ሲጋራ አጨሳለሁ ላንቺ ስል ላንቺ ስል
በየወረቀቱ አገኝሽ ይመስል

ሳስብሽ አድራለሁ አንቺን ሳሰላስል
ናፍቆት ከውለታ ይቆጠር ይመስል

ሳታደላድይዉ አፋፍ ላይ ሰርተሽ
ወዶ ገደል ገባ ታሰኝኛለሽ

ሳይህ ሳይህ ውየ ሳልጠግብህ ይመሻል
ይኸስ ትልቅ ጠንቋይ አይነ ጥላ ያሻል

ስሄድ ስሄድ ውየ ስሄድ ስሄድ ነጋ
ጅብ አይበላም ቢሉኝ የናፋቂ ስጋ

ስምህን እንዳልጠራው ይበላዋል ቡዳ
እንዳው በሆዴ ውስጥ የእኔ እዳ የእኔ እዳ

ስምሽን እንዳልጠራው ያውቁብኛል ብየ
ፅጌረዳየ አልኩሽ በአበባ አስመስየ

ስምሽን እንዳልጠራው ያውቃሉ ሰዎቹ
እንደው በሆዴ ውስጥ የኔ አመለ ምቹ

ስትቀሪ እቀራለሁ አላዋልልሽም
በሴት ሴት ይተካል እናቴ አይደለሽም

ስንቱን ማጣት ችየ ዝናየ ሲነገር
ከእንክርዳዱ ብሶ አሰከረኝ ነገር

ስንቱን በመትረየስ ብየ ልጨርሰው
ስንቱን በዲሞፍተር ብየ ልጨርሰው
አይኗ እያጣቀሰ የሚያመጣውን ሰው
ጥርሷ እየተጣራ የሚያመጣውን ሰው

ስንዴው ዘረዘረ ወፎቹ በሉት
ከምን ይቆጠራል ተጣልቶ ናፍቆት

ስወድህ ውደደኝ ምን ይለጥጥሃል
እንደኔው ሰው እንጂ ማን መልአክ ወልዶሃል

ስጡኝ የአረብ ሰንጢ ግንባሬን ልቆራ
ስለተጋደሙ መች ይገጥማል ገላ

## ሸ

ሸህ አባድር መጀን አምስቱ በረኛ
አራት ወሎ መጀን ዱበርቴየ አደራ
አዙር አሽከርክሮ ይጣልሽ ወደኛ

ሸሚዜንም እንኩ ሱሪየንም እንኩ
የአደባባይ ልብሴን ያቺን ልጅ አትንኩ

ሸሞንሟና ቀሚስ አሰፍቸልሽ
ሸሞንሟና ጥለት አስቋጥሬልሽ
ሸሞንሟና ኩታ አስፈትየልሽ
የማንን ግትልትል ትጎትቻለሽ?

ሸንበቆ ቢረዝም ጅብ አያንጠለጥል
የዚያችና የዚች ጣእማቸው እየቅል

ሸዋ ላይ ቆንጆ አይቶ ሊያብድ ነው ሰውየው
ጎጃም ላይ ጥርስ አይቶ ሊያብድ ነው ሰውየው
አርሲ ላይ ጡት አይቶ ሊያብድ ነው ሰውየው
ሃረርጌ ዳሌ አይቶ ሊያብድ ነው ሰውየው
ትግራይ ሹርባ አይቶ ሊያብድ ነው ሰውየው
አምጡት ይለይለት ወሎን እናሳየው

ሸጋ ልጅ አርግዛ ጠንቶባታል ምጡ
እሷም እህ ትላለች እናንተም አዳምጡ

ሸጋ ልጅ አርግዤ ከነቁመናው
ሸዋ ተጨነቀ እንዴት ልውለደው

ሸጋ የወለደ ዘሩ ሸጋ ይሁን
ቆንጆ የወለደ ዘሩ ቆንጆ ይሁን
ጧት የወጣ ልቤ አልገባም እስካሁን

ሺ ምጣድ ተጥዶ አልሞቅ አለ ቤቱ
ብርድ እንዲህ የገባን ምንድነው ምክንያቱ?

ሸሙንምን ሸሙንሙን ሸሙንሙን በይልኝ
የያዘኝ በሽታ ገለል እንዲልልኝ

ሸማግሌ አገባሁ ሸበቱን ነቅየ
ሲወጣ ሲገባ ቢመርቀኝ ብየ

ሸምብራ ዱቤውን የበላው ሌላ ነው
እኛ የታማነው በጥርጣሬ ነው

ሸሽግ አርጌ ነው እኔሷን መውደዴ
የተሰማ እንደሆን ክረምት ያህላል ጉዴ

ሸቶ መግዛትም ጎንደርም ያውቃሉ
ሸቶ መግዛትማ ጎጃሞች ያውቃሉ
አፍንጫው ወሎ ነው በምን ያሸታሉ
ሸንጧ እሚጎተተው እንደ ሰላሌ ጉም
ጀመረ ባላገር ነገር ሊያልጎመጉም

## ቀ

ቀለባችን ሁሉ አለቀ በስለት
ምን ይበላ ይሆን የተገናኘን ለት

ቀና ብየ ባየው ቋንጣው መነመነ
አሁን የት ይገኛል ከአንቺ የታመነ?

ቀንም ተቀምጨ አለቃቅሳለሁ
ማታም ጋደም ብየ አለቃቅሳለሁ
አንቺንም አይኔንም አጥቼው አርፋለሁ

ቁልቢ ገብርኤልን ትስማለህ አሉ
መፀደቁ ነው ወይ ሰው እየገደሉ

ቁሚልኝ ቁሚልኝ እንደማስብሽ
ሁሌም ያገሬ ልጅ ወገኔ ሆነሽ

ቁና ጥሬ ልብላ አመት ልመንን
እሷን በሱባኤ አገኝ እንደሆን

ቁጭ በይ እናውጋ ቁሚ እንጎራደድ
ሰው አለ ሰው የለም አያሰኝም መውደድ

ቁጭ በይ ከድንኩ ሂጅ ይመሽብሻል
በልብሽ ውደጅኝ ባይንሽ ያውቁብሻል

ቁጭ ብየ ግራዋ ቆሜ ኮሶ ጠጣሁ
እንዳንቺ መለየት የመረረኝ አጣሁ

ቃሉም ገበያ ነው ለገሰገሰ ሰው
ባቲም ገበያ ነው እግር ላደረሰው
ሁልጊዜ ባንቻሮ እንዴት ይኖራል ሰው

ቃሉ ተሁለደሬ መሃል አገር ወሎ
የናፈቀማ ሰው ይመጣል ኮብልሎ
እናቴን አባቴን ወንድሜን አይ ብሎ
ቃሉ ተሁለደሬ ወባ ረፈረፈው
በጧት ሚች እሷ ነች እግሯ የማያርፈው

ቄሱስ ምን ቄስ ናቸው ዳኛውስ ምን ዳኛ
የሰው ባል አትንኩ የሚሉ አማርኛ

ቅጠል ቆረጠና መድሃኒት ነው አለኝ
ማተቡን ፈታና ፍቺ አንገትሽን አለኝ
ምነው ሆዴ ፈራ ሊቀር ነው መሰለኝ

16

## በ

በሉ እስኪ እንጫወት እንጫወት ዛሬ
ነገማ ስራ ነው ይጠመዳል በሬ

በላሁት በላሁት እንጀቱን በላሁት
ወስከምባ ከሌለው ክፍቱን ካገኘሁት

በል ተጫወትብኝ ተወዳጅ መስለህ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ ሲከፋኝ አይተህ

በልቼ ርቦኛል ጠጥቼ ጠምቶኛል
ጠላቴ ትዝታን ማን ሰው ያስጥለኛል

በል እራሴን በለኝ እንካ ዘነዘና
በአንተ የተነሳ አብዳለሁኝ ገና

በል እንባየ ውረድ ደረቴን ግመሰው
ዋ ብሎ ለመቅረት ይገናኛል ወይ ሰው?

በል እደር ጆሮየ ነገ እቆርጥሃለሁ
በአንተም ክፉ ነገር ሰምቼብሃለሁ

በመቅላት አይደለ በመጥቆር አይደለ
በመርዘም አይደለ በማጠር አይደለ
በውፍረት አይደለ በመቅጠን አይደለ
ትክ ብለው ሲያዩት አስደንጋጭ ሰው አለ

በሬ ጥጃ ወልዶ ተኝቶ ይልሳል
እንኳን የአንቺ ፍቅር የእናት ሞት ይረሳል

በሰማይ የሚፀድቅ በምድር ያስታውቃል

ከከንፈሩ ተርፎ ጥርሱ ጣይ ይሞቃል

በሰብል መሃከል አግዳ ብዙ ላም
ምን አይነቷ ልጅ ነች እህል አታሰበላም

በሴቶቹ ሁሉ ምን አዞርሽባቸው
እንቺን አልመስል አሉኝ ባያቸው ባያቸው

በስመ አብ በስማም አልኩኝ ሰይጣኑን ፈርቼ
ብዙ የለመድኩት ብቻየን ቀርቼ

በስምንተኛው ሽ ሰው በረከሰበት
እኔውም እብድ ነኝ አንተን ያመንኩበት

በስንቡል በሽቶ መች እጠቡኝ ይላል
እመር ያለው ገላ እንዲያው ደርሶ ያምራል

በሸዋ በጎንደር ቆንጆ አይቼ አለፍኩኝ
በጎጃም በባሌ ቆንጆ አይቼ አለፍኩኝ
እወሎ ላይ ስደርስ ልቤን አስረከብኩኝ

በሽተኛው በዛ መድሃኒት አነሰው
አሁን የት ይገኛል ያልተለከፈ ሰው

በቃ በሩን ዝጉት ከቀረ ልማዴ
ተከፍቶ ማደሩን አይወደውም ሆዴ

በቅሎ የለው ፈረስ ሙልጭ ያለ ድሃ ስትለኝ ሰማኋት
በእግረኝነቴ ነው እሷን ያገኘት

በቅሎየ ስገሪ እንግባ አገራችን
የወጣንበቱ ሞልቷል ጉዳያችን

በቅሎየ አትስገሪ ላንገባ አገራችን
የወጣንበቱ ይሙላ ጉዳያችን

በነጋ በጠባ ስም ይወጣል ወይ
አንዴ ቆንጅትየ ብየሽ የለም ወይ?

በነጠላ ጫማ በእንቺ አረማመድ

17

እንዴት አለቀልሽ የቸርችል መንገድ?

በነጫጭ ዶሮ እየተመሃኘ
በጥቋቁር ዶሮ እየተመሃኘ
በቀያይ ዶሮ እየተመሃኘ
በገብስማ ዶሮ እየተመሃኘ
የኔማ በሽታ ሰው ሆኖ ተገኘ

በአለቅሰው በአለቅሰው አይኔ አመል አወጣ
ከወዲህ ሰው ላይቀር ከወዲያ ላይመጣ

በአምሳም በሰላሳም ሲገዛ ፈረስ
በመቶ ብር ገዛሁ የሰው አጋሰስ

በአባቱ መሬት ላይ የተኛውን በሬ
ተንኩሰው ነካክተው አደረጉት አውሬ

በአንቺ አለመታመን በሰው ሌብነት
በይ እስኪ ስጋየን አስወስጂው ድመት

በአንቺ የሚጨክን ምን አንጀት ነበረኝ
ነገር ወዲያ ወዲህ ሆነና ቸገረኝ

በእናቴም የለብኝ በአባቴም የለብኝ
አይኔ ቡዳ ሆኖ የሰው ልጅ በላብኝ

በእናቷ ጓያ ነች በአባቷ ባቄላ
የሁለት ጥሬ ልጅ እንደምን ትበላ

በከንቱ ነው እንጂ አደራ የአልኩሽ
ማን ይለቅልኛል እንደ እኔ ያየሽ

በዛ በበረሃ በዛ በፀሃይ
እቱ ጥላ ይዤ ልከተልሽ ወይ?

በዛ በጎዳና በዛ በሸርተቴ
እጥፍ ዘርጋ እያለ መጣልሽ አንጀቴ

በዛ በጠራራ ለምን ነው መንደዴ

**እረ ጥላ ጥላ ቁረጥልኝ ሆዴ**

**በይ ተይው በይ ተይው በይ ተይው አይጎዳም**
**አንቺን እንደ ጭምት እኔን እንደ ሆዳም**

**በደልህ በደልህ በደልህ ልክ የለው**
**መልኼ አስታወስኩህ ለልቤ ልብ የለው**

**በደም ተቀላቅሎ አንጀት የሚያማስል**
**የልቤ ቅኝቱ ተገኝቷል አምባሰል**



**በጣም የሚያስከፋ ምን ተናገርኩት**
**ያንን ጋራ ዙረህ ተመለስ በሉት**

**በጦሳ ተራራ በዚያ በሽርተቴ**
**እጥፍ ዘርጋ እያለ መጣልሽ አንጀቴ**

**በጨለማ ስሄድ ማነህ ይለኛል ሰው**
**ሰርቄ አይደለም ወይ የምመላለሰው**

**ቡሃቃ እንኳን የለኝ አንጉቼ አላጎርሰው**
**ይብላኝ እኔን እኔን ተርቧል ይኸ ሰው**

**ቢሻኝ ደሴ ልሂድ ቢሻኝ መርሃ ቤቴ**
**ጅምሬን ማን ነክቷት ሳይሰማ ሞቴ**

**ቢያምሽ ታመምኩልሽ ቢመቱሽ ደም ወጣኝ**
**ብትሞችስ አልሞትም ድሃው ምን በወጣኝ**

**ባልም አላገባ ጨውም አልደቁስ**
**እንዲሁ እኖራለሁ የሰው ቤት ሳጤስ**

**ባልሽን እሰሪ እንጂ በጭራ ገመድ**
**እኔ ከንጉስ አገር የታባሽ ልሂድ**

**ባልንጀራ ማለት የወገብ ሽጉጥ ነው**
**ወንድም የሚደርሰው ደም ከደረቀ ነው**

ባል ያላችሁ ሁሉ ክተቱ በጎታ
አልከለከልም የእግዜር ጋለሞታ

ባቲ አንቻሮ ቃሉ በሶስቱም መንደር
የሸማግሌ ልጅ ተብየ ነበር
እይው በአንቺ በኩል ስሜ ሲደፈር

ባቲ ገበያ ላይ ቅል ይዤ እንደ ለማኝ
እሷን ሳላገኝሁ ገበያው ሳልቀናኝ

ባቲ ገበያ ላይ ፈለኳት የለችም
አምባሰል ገበያ ፈለኳት የለችም
ምን አይነቷ ልጅ ነች ለፍቅር አትመቺም

ባቲ ጎድጓዳ ነው አይታይም ጢሱ
የማትቀር ልጅ ቀረች እስኪ እጣን አጢሱ

ባትሪ ድንጋይ የለኝ ኩራዝ አላበራ
ፍቅሬ ሳቅ በይና አንዴ ራቴን ልብላ

ባቷና ደረቷ ስጋው ተነባብሮ
ወገቧ ቀጭን ነው አልበላም ወይ አብሮ

ቤሳ ምላጭ ይዘሽ ከሆዴ ገብተሽ
ኧረ ተይ አንጀቴን ትቆርጭዋለሽ

ቤቴን እሰራለሁ ጦሳ ጋር ላይ
በነጋ በጠባ ላይ ደሴን እንዳይ

ቤትሽና ቤቴ ማዶ ለማዶ ነው
ታዲያ ምን ይሆናል የአንቺ ባለአጥር ነው

ቤትሽና ቤቴ አግድመት ለአግድመት
አንገቴ ጠመመ ስጋ እንዳየ ድመት

ቤትሽ እመንገድ ዳር ቢጠሩሽ አትሰሚ
ስምሽ አይደለም ወይ ትርንጎና ሎሚ

ቤት አሰራሽ አሉ ትልቅ አዳራሽ
አሞራሽ እኔ ነኝ የማፈርስልሽ

ብላጨው አመመኝ ብሰራው ከፋኝ
አንድ እራሴ እኮ ነው የሚያስጨንቀኝ


20

ብርቱካን በልቼ ሎሚ ሎሚ አገሳኝ
አንቺ እንደምን አለሽ እኔስ ልቤን ነሳኝ

ብርቱካን ነሽ አሉ የምትመጠጭ
ከሆዴ ገብተሻል አርፈሽ ተቀመጭ

ብስ ብስ ቢሏት የማትሰማ ድመት
ሚዛኑን ደፋችው ሳንለካካበት

ብተኛ እንቅልፍ የለኝ ብሄድ አላፈጥን
እንደ ቀጭን ኩታ አንቺን ሳፍተለትል

ብትሄጂ እሄዳለሁ አላዋልልሽም
በሴት ሴት ይተካል እናቴ አይደለሽም

ብትሞቺ እሞታለሁ አላልከኝም ወይ
እንኳን ልትሞትልኝ ታመምክልኝ ወይ?

ብትወደኝ ልወድህ ማላ ነበረብኝ
ስትጠላኝ ብጠላህ ምን ኩነኔ አለብኝ

ብወዳት ነው እንጂ የማነክሰው
እኔ ራሴን ችየ ቆሜ እምሄድ ሰው

**ቦረና ቦረና ቦረና ገነቴ**
**አብረከረከችኝ ገባች በጉልበቴ**

## ተ

ተማምለን ነበር እንዳናንቀላፋ
ተኝተህ ተገኘህ መተማመን ጠፋ

ተረከዘ ሎሚ ጠብደል ያለ ባት
ኮራ ያለ ዳሌ ጎተት ያለ አንጀት
ከሷ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት
ለአፈር አይደለም ወይ የተሰራሁት

ተረከዝ ሎሚ ተይ ይፈርጥብሻል
እኔን ጫማ አድርገሽ ብትሄጅ ይሻልሻል


21

ተራራው ተንዶ ተይዟል በገመድ
ወደ አንች እሚያመጣኝ ወይ ዘመድ ወይ ዘመድ

ተስማማ እነደ እንጀራ ጣፍጥ እንደጠጅ
ያገር ልጅ ይሻላል ቢከፋም ቢበጅ

ተኛ ባሉኝ ተኛሁ ቀሰቀሱኝ ነቃሁ
ምን ጊዜ ከብሬ ለመወረስ በቃሁ?



ተቻችሎ መኖር ነበር ወግ ማእረጉ
የያዙት ይጠፋል ሌላ ሲፈልጉ

ተኝቼ ላልተኛሁ መባነኑ ባሰኝ
ወየት ላይ ሆና ነው የምትቀሰቅሰኝ?

ተከለከለ አሉ የአንቺ አደባባይ
ካገኘሁ ማለፊያ እኔ አልመጣም ወይ?

ተከለከለ አሉ ደጅሽ በምስለኔ
እንዴት እሆናለሁ ልማደኛሽ እኔ

ተከዜን አልፌ ሊማ ሊሞ ስደርስ
ያስጋልበኝ ጀመር የትዝታው ፈረስ

ተኩሰው ላይመቱ ተሚግተው ላይረቱ
የተኛውን በሬ ቀሰቀሱት ከንቱ

ተኳሽ እወዳለሁ መራኸኙም አልጠላ
ሲደክመኝ አርፋለሁ ከጎፈሬው ጥላ

ተወኝ ትቻሃለሁ ረሳሁህ እርሳኝ
እንዳሮጌ ቁና እየጣልክ አታንሳኝ

ተወያይተን ነበር ውል ያለው ነገር
ተይው ከዘነጋሽ ከረሳሽ ይቅር

ተወደድኩኝ ብለህ አትበል ደንበር ገተር
እኛም የዚያን ሰሞን እንዲህ አርጎን ነበር

ተወደድሽ እያሉ ይሉኛል ሃይ ሃይ
ሊያንከራትቱኝ ነው እንደ ግሩም ሻይ

ተዋት ተዋት አሉኝ ዘመዶቼ ሁሉ
እንደእኔ መች አዩት ሰውነቷን ሁሉ

ተዋዶ ተዋዶ መጣላት ሲመጣ
አንደዜ ኩፍኝ ነኝ አንደዜ ፈንጣጣ

ተዋዶ ተዋዶ የመጨረሻው
ይህ ሰው ምን ይመስላል ሆነ ማርከሻው

ተው ልቤ ተው ልቤ ገደል ትገባለህ
ከአለው ልመድ እንጂ ከቀረው ምን አለህ?

ተው ልቤን ላክልኝ ማታ በጨረቃ
ጌቶቹ ተቆጡኝ እየረሳሁ እቃ

ተው ማነህ ተው ማነህ ተው ማነህ ተው ማነህ
የተኛ ሰው አለ ትቀሰቅሳለህ

ተው ማነህ ተው ማነህ ተው ማነህ ተው ማነህ
የተኛውን ልቤን ትቀሰቅሳለህ

ተውት አትከልክሉት ወንዙን ይሻገረው
ዞሮ ይመለሳል ነገሩ ኩርፊያ ነው

ተውኝ እባካችሁ እንደራስ ነው ፍርድ
ጭምት ያሳብዳል ዛርና መውደድ

ተው የአገሬ ውሃ አረንጓዴ አትልበስ
እጠጣህ ይሆናል ምናልባት ብመለስ

ተው ያሉህ እንደሆን በል ያሉህ ይመስል
ትወዳለህ ወደል ትጭናት ይመስል

ተይኝ ትቼሻለሁ ረሳሁሽ እርሺኝ
እኔ ለአንቺ አልሆንኩሽ አንቺ ለእኔ አልሆንሺኝ

ተይኝ አላልኩም ወይ ተኳኩሎ ሜዳ

አይን ወረተኛ ነው ያመጣል እንግዳ

ተይኝ አላልኩም ወይ ይህን ነገርሽን
ጭድ እንዳየ በሬ ጓሮ መዞርሽን
ጭድ ያየ በሬ እንኳን ጎርሶ ይመለሳል
አንቺ ከመሄድሽ መያዝሽ ይብሳል

ተይ አይሆንም ስልሽ ይሆናል ብለሽኝ
አንቺም ግራ ይግባሽ ግራ እንዳጋባሽኝ

ተይ እንዲህ አይደለም መች እንዲህ ሆነና
ሰው ወዶ ሲጠሉት ያስቸግራልና

ተደፍቼ ላልቅስ ከጉልበቴ ላይ
ልብም እንደ ሸክላ ይሰበራል ወይ
ምነው አይሰበር አይንኮታኮት
በነጋ በጠባ ከተከዙበት

ተጨዋውተን ነበር ውል ያለው ነገር
ተይው ከዘነጋሽ ከረሳሽ ይቅር

ታምሜ ታምሜ ሲጠናብኝ አይተሽ
ወዴት ነው ምትሄጂው ሬሳ ዘርግተሽ
እኔን ማጣጠቡን መገነዙን ትተሽ

ታርሶም ተሸምቶም ይበላል እንጀራ
እንደምነሽ ጥቃት የሞት ባልንጀራ

ታከመው ይሉኛል እንግዲህ ምኑን
እንደተወጋሁኝ የቀረሁትን

ታይታ እማትታለፍ ቆንጆ ልጅ ነበረች
ተመልካች በዛና በቃ ተውኩት ቀረች

ትልቁን አጎዛ ሸጠችው በብር
ትንሽ ለምድ አመጣች የማያድኑር

ትመጫለሽ ብየ መንገዱን አላምነው
የሚመላለሰው አህያና ላም ነው
ትመጫለሽ እያልኩ ማዶ ማዶ ሳይ


24

አንቺየ ጨክነሽ መቅረትሽ ነው ወይ?

ትመጫለሽ እያልኩ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ
የልጅነት አይኔ ሟሟ እንደ በረዶ

ትመጭ እንደሁ ልምጣ ትቀሪ እንደሁ ልቅር
ሰው ልከሽ ሰው ልኬ ይሆናል ወይ ፍቅር?

ትመጭ እንደሁ ልምጣ አላዋልልሽም
በሴት ሴት ይተካል እናቴ አይደለሽም

ትተነው ነበረ አምናና ሃች አምና
ተመልሶ መጣ ፍቅር እንደ ገና

ትተኩሱ እንደሆን አይታችሁ ተኩሱ
ለአልረባ ግርግር ሰው አታስጨርሱ

ትተኩሱ እንደሆን ተኩሱ እያያችሁ
ለአልረባ ግርግር ሰው ታስፈጃላችሁ

ትቼህ ረስቼህ ሆኘ እንደነገሬ
በምን አስታውሼህ ሲያመኝ ዋለ ዛሬ

ትናንትና ማታ በደጅሽ አልፌ
ልቤን ትቼው መጣሁ ሳምባየን ታቅፌ

ትናንትና ማታ አይኔማ አንቺን አይቶ
ሲያለቅስ አመሸ በጢስ አመሃኝቶ

ትናንትና ማታ ዛሬ ለሊት በልሜ
ምሰሶው ተሰብሮ እባህር ላይ ቆሜ
ምሰሶውም አንቺ ባህሩም እንባየ
እንደተለያየን ቀረን ወይ ደህናየ

ትንሽ ልጅ ወድጄ እንጥል የምታህል
እንኳን ከሰውና አጣላችኝ ከእህል

ትንሽ ገብስ አምጥተን ቁይልን ብንላት
ይች የባላገር ልጅ የምታምሰው ናት

ትዝታህን ውሰድ ለእኔም አስቸገረኝ
እሰው ጋር ስጫወት እያደናገረኝ

ትዝታህን ውሰድ ብለሽ የላክሽብኝ
አንችው ጋር ይቀመጥ እኔም የአንቺ አለብኝ

ትዳርም አልይዝም ለአሳብም አልቸኩል
የእነእሜትየን ባል እይዛለሁ የእኩል

ትግሬን እንዳልሰጥሽ የአፄ ዩሃንስ ነው
ወሎን እንዳልሰጥሽ የንጉስ ሚካኤል ነው
ሸዋን እንዳልሰጥሽ የአፄ ምኒልክ ነው
ከልቤ ተቀመጭ የኔ አገር እሱ ነው

ቶሎ ቶሎ ብየ ልውጣው አቀበቱን
ልብ ያሰበው ነገር አይገኝ እለቱን

## ነ

ነጭ ነው ዘንጋዳው ቀይ ነው ዱቄቱ
ተጣልቶ መታረቅ አይሆን እንደ ጥንቱ

ነጭ አሞራ በርሮ ይገባል ከዋሻ
ሰው ነገረኛ እኔ ሆደ ባሻ

ነጭ ጤፍ እንጀራ በአዋዜ ብትን
ጥርግ አርጎ መብላት የታሙበትን

ነግሬሽ ነግሬሽ መጨረሻው ጥል ነው
ልብ ይሰማል እንጂ ጆሮማ ቅጥል ነው

ና ብትይኝ መጣሁ ብመጣ አጣሁሽ
በእድሌ አዘንኩ እንጂ መች ተቆጣሁሽ

ና ግባ ተጫወት ኩርፍታው ምንድን ነው
የከሳሁ የጠቆርኩ ባንተው ትዝታ ነው

# አ

አሁን ምን ያደርጋል አምባሰል መቃኘት
በፊት ነበር እንጂ ተሸሎ መገኘት

አሁን ምን ይሉታል ፈሪ ማጠንጠኑ
ቅጠል ሳይበጠስ ካልደረሰ ቀኑ

አሁን እዛ ሆነሽ የምትታይኝ
እንድመጣ ነው ወይ ጅብ እንዲበላኝ?

አሁን ከቅድሙ ትንሽ ተሻለኝ
የአራት ኪሎ ልጆች መጡ መሰለኝ

አሁን የት ይገኛል እንደ ፍቅር ልጅ
ቢኮሩ አያስኮራ ቢያረጁ አያስረጅ

አሁን የእኔ አሟሟት አሟሟት ነው ወይ
ቁጭ ቁጭ ያለ ጡት አንድ ቀን ሳላይ

አሁን ፍቅር ቢሞት ማን ይገንዘዋል
ሁሉን በየቤቱ ይወዘውዘዋል

አለ መዘዝ መዘዝ ሊበላኝ እባቡ
ቆማ ታስቀብረኝ በሷ ነው ሰበቡ

አለቃቅስ ነበር አላለቅስም ተውኩት
እናፍቅ ነበረ መናፈቁን ተውኩት
የሳጡት ይደርቃል እንኳን የቆረጡት

አለቦታው ገብቶ አለ ዘገባው
አሳዘነኝ ልቤ የተንገላታው

አለች እረብ እረብ ወገቧ ሊሰበር
አልጋው ስንገዛው ሽቦው ደህና ነበር

አላመጣው የለኝ አልቀላውጠው
ዛሬስ ከነባሏ ልትናፍቀኝ ነው



27

አላማጣ ውየ መልሼ አላማጣ
በበሽታየ ላይ በሽታ ላመጣ

አላሰራሽም ወይ ደጃፍ ለቤትሽ
ወለል ብሎ ታየኝ ሳንቃው ደረትሽ

አላሳይህም ወይ እርቅናየን ቆሜ
ምን አከላት አለኝ ከአንተ የተለየ

አልመጣም ቀረሁኝ አልመጣም ቀረሁኝ
ከአንቺ የበለጠ እዚህ አገኘሁኝ

አልቆጣም ነበር አላኮርፍም ነበር
እንዲህ መናፈቄን አውቄው በነበር

አልበላም አልጠጣም አልሻም ይቅርብኝ
እሷን ብቻ አልጣ የአይን ርሃብ አለብኝ

አልታይህ አለኝ የአገሬ ሰማይ
እንደዚህ እርቄ ሄጃለሁኝ ወይ?

አልታጠበውም ይብላኝ ጭቅቅት
እግሬ ደመኛየ ሆኖ አገኘሁት

አልታጠበውም ጭቅቅት ይውረሰኝ
ይህ እግሬ አይደለም ወይ ከሷ ያደረሰኝ

አልነገርሽኝም ወይ ባላባት ነኝ ብለሽ
ታዲያ ምን ሆነሻል እዚህ አገር የለሽ?

አልኩኝ ብድግ ብድግ ዘንድሮስ ቀለለኝ
አንጀቴን አውጥተሽ በላሽው መሰለኝ

አልወራረድም እኔ በፈረስ
በዛች ልጅ ቁንጅና በዛች ልጅ ጥርስ

አልወራረድም እኔ አልገባም እዳ
ሸንጧ የሚመስለው የሰላሌን ሜዳ

አልጋውም በቂ ነው ነቱም አላነሰኝ
ደህና ተኝቻለሁ ሰው ካልቀሰቀሰኝ

አልግደረደርም ይወደዋል ሆዴ
ማነው የነካብኝ ሽንጡን በጎራዴ

አመለ ልክስክስ አመለ ውዳቂ
ሰንጋ ፈረስ አስሮ አህያ ናፋቂ

አመለኛ በቅሎ ልጓም ያላምጣል
ወደድሽኝ ወደድኩሽ ጠላሁ ምን ይመጣል?

አመለኛው እግሬ መመሄድ የለመደ
ሃይቅን ሲዞር  ውሎ ውጫሌ ወረደ

አመት ሁለት አመት ይቀመጣል ጠጅ
መናፈቁ አይቀርም የራቁት ወዳጅ

አመት ሁለት አመት ይቀመጣል ጠጅ
የወደደ አይሞትም ይታመማል እንጂ

አሙን አሙንና ወቀጡን እንደ ገብስ
ይተውን የለም ወይ የልባቸው ሲደርስ

አሜተኛም ይማ ለዋሽም ይለውሰ
እጅዋን በጄ ይዤ እጮሃለሁ ለንጉስ

አምላክ አቤት አቤት እግዜር አቤት አቤት
የሰማዩ ጌታ የምድሩ ባለቤት
የምወዳትን ልጅ አርግልኝ ጎረቤት

አምላክ አቤት አቤት የምለምንህን
የአጣ ሰው ሳያገኝ አይሙት እባክህን

አምስት መቶ ፍራንክ ስድስት መቶ ብር
መቅለጡንስ ቅለጭ ለማን ልናገር

አምስት መቶ ፍቅር ሶስት መቶ ትዝታ
የምችለው ስጠኝ አቤት የኔ ጌታ


29

አምባሰል ላይ ሆኖ ይታያል ርቄ
እየተበሳጨሁ ቀረ መናፈቄ

አምባሰል ማርየ ብዙ ሃብት አላት
እኔን ይዞ መብላት እንዴት አቃታት?

አምባሰል ማርየ ነሽ ወይ ወረባቦ
መጣልሽ ፍለጋ ልቤ አንቺን ተርቦ

አምባሰል በገደል መቾ ያሽሟጥጡታል
ፈረስ ባያስጋልብ ማር ይቆርጡበታል

አምባሰል በገደል መች ያሽሟጥጡታል
ፈረስ ባያስጋልብ ሰው ይወጣበታል

አምባሰል ተንዶ ግሽን ደግፎታል
አምባሰል መናዱ ቃልሽ መፍረሱ ነው
ግሽን መደገፉ የኔ ደግነት ነው

አምባሰል ዳመና የጁ ፀሃይ ነው
መጣ ትዝታዋ የሚጋረደው

አምናና ሃች አምና ሁለቱን አመት
አንቺ ነሽ በልቤ የከረምሽበት

አምናና ሃች አምና ደህና ሰው ነበረች
በሽታዋ መጣ ትተኩስ ጀመረች

አምጡልኝ ሽጉጤን እስኪ ልተኩሰው
ከእንግዲህ ሽሽቼ የማላመልጥ ሰው

አምጡ ጥቁር ልብሴን እስኪ ይመርብኝ
ይህ ወዶ መለየት ተደጋገመብኝ

አሞራ በሰማይ ይላል ዳኛ ዳኛ
የበደለ ክሶ እንታረቅ እኛ

አሞራ ወድጄ አሞራ ሆኛለሁ
ከየትኛው ዛፍ ላይ ባርፍ አገኝሻለሁ

አሞኝ እንደዋለ አሞኝ ሊያድር ነው ወይ?
ይኸ ሰርቶ መብላት ጤና ላይሆን ነው ወይ?

አረገዝኩ እንዳልል ሰው አልደረሰብኝ
ሸጋ ልጅ በሆዴ ሸር ጉድ አለብኝ

አራዳ ጊዮርጊስ ትሳያለሽ አሉ
መፀደቁ ነው ወይ ሰው እየገደሉ

አርሜ ኮትኩቼ የሎሚ ዘንጌን
መልከኛ ወሰዳት ወይ ገባር መሆን

አርሜ ኮትኩቼ ስጠባበቅሽ
እናትሽ ክፉ ሰው በበአል አጨዱሽ

አርሶም ተሸምቶም ይበላል እንጀራ
እንደምነሽ ጥቃት የሞት ባልንጀራ

አርዳኝ ጥላኝ ሄደች ዘልዝላ ዘልዝላ
ከእንግዲህ ተነስቶ ሰው አይሆንም ብላ

አርጉት ደመቅ ደመቅ አይቀዝቅዝ ቤታችን
ለሰው እንተርፋለን እንኳን ለራሳችን

አርጊኝ አቀፍ አቀፍ አርጊኝ ሳም ሳም
እናት እንደሌለው እንደ ስስታም

አርጊኝና ልሂድ ከጎፈሬሽ ላይ
ከአደሱ ከቅቤው እከብዳለሁ ወይ?
ከአደሱ ከቅቤው ምን ትከብደኛለህ
አገሩ በረሃ ትቀልጥብኛለህ

አሰሱን ገሰሱን ልመድልኝ ሆዴ
መገበሪያ ሆኗል አልተገኘም ስንዴ

አሰሱን ገሰሱን ከማግበሳበሱ
መቀመጥ ይሻላል ሰው እያስታወሱ

አሳ በቢርቢራ የሚያጠምድ ጠፍቶ
ያሳማት ያሳማት ያሳማት ተኝቶ

አሳ አበላሻለሁ አባይ ዳር ነው ቤቴ
ዶሮ መረቅማ ከወዴት አባቴ

አሳ እንኳን ይሄዳል አረንጓዴ ለብሶ
ምነው ብንታማ የልባችን ደርሶ

አሳዘነኝ ልቤ የተንገላታው
አለቦታው ገብቶ አለ ዘገባው

አሳድሮ ልቤ ዛሬ ነገ እያለ
ተከፍቶ ብናየው በሆዴ ስንት አለ

አስለምዶኝ ነበር የማታ ጨዋታ
እያንጎራጎረ ክራር እየመታ

አስሩንም ጣቴን ቢላወ ቆርጦኛል
አትንኩ ያቺን ልጅ ያንገበግበኛል

አስነክተሸኛል ቅጠል ምናምን
እንዲህ አያደርግም ፍቅር ብቻውን

አስነክተኸኛል መድሃኒት በጠላ
አንተን አስወድዶ ሌላ የሚያስጠላ

አሸዋ ፍጭ አሉኝ የማይልመውን
ድንጋይ ቀቅል አሉኝ የማይበስለውን
ያቺን ልጅ ተው አሉኝ የማይሆነውን

አሻቅቤ ልሂድ አግድሜ ልጣሰው
ሲያቀብጠኝ ወድጄ ይፋ እማይወጣ ሰው

አሻግሬ እያየሁ ማዶ ማዶውን
አይኔ ድር አደራ ያልፈተለውን

አቀበት ስወጣ ላብ እያጠመቀኝ
ቁልቁለቱን ስወርድ እንባየ እያነቀኝ
መቅረቱን አትቀሪም እስከዛው ጨነቀኝ


32

አቀበት ቁልቁለት ይሰግራል በቅሎሽ
ተፈናጧል ልቤ ትጥይዋለሽ

አቃጠሉት አሉ ያለሽበትን
ሰው እጠይቃለሁ አረሽ እንደሆን

አበደች ይሉኛል የት ላይ ነው ማበዴ
ከድፍን አገር ሰው አንድ አንተን መውደዴ

አበድኩ አበድኩና እንግዲህ ልጨምት
የልጆቼን እራት ማሽላ ልሽምት

አበጀች በላችው ወንዱን ልጅ በእሸቱ
እንግዲህ በቃርሚያው ይተራመስ ሴቱ

አባታችን ሰፈር ይመዘዛል ሃረግ
ባላገኝሽ እንኳን በስምሽ ልረግረግ

አባት አልረገመኝ እናት አልረገመኝ
ይኸ ብቻ ማደር ምነው ደጋገመኝ

አባቷ ክፉ ሰው የሰማይ እሳት
እናቷ ክፉ ሴት የበቅሎ ቁርጠት
ልጂቱ ገዳዳ ቆማ አትጫወት
አመንኩሷት እንጂ ቀሚሷን ቀዳችሁ
መቼም ሰው አትሆንም እናንተ እያላችሁ

አባቷ ቢመጡ በሬየን አረድኩኝ
እናቷ ቢመጡ ላሚቱን አረድኩኝ
ወንድሟ ቢመጣ ወይፈኔን አረድኩኝ
እህቷ  ብትመጣ ጊደሬን አረድኩኝ
እሷ መጣች ቢሉኝ እኔው ተጋደምኩኝ

አባቷን ባስጠይቅ እናቷን አሉኝ
እናቷን ባስጠይቅ ወንድሟን አሉኝ
ወንድሟን ባስጠይቅ እህቷን አሉኝ
እህቷን ባስጠይቅ አክስቷን አሉኝ
አክስቷና ባስጠይቅ አጎቷን አሉኝ
አጎቷን ባስጠይቅ አያቷን አሉኝ
አሁን ምን ያደርጋል ነገር መስቃቀም
በአባት ሳላገኛት በአያት ምን ልጠቀም

አባካኝ ይለኛል አባካኝስ እሱ
እያብከነከነኝ በአይንና በጥረሱ

**አባይ ቤት የሰራ በወዳጅ የኮራ
ሁለቱ አንድ ናቸው በሞኞቹ ተራ
አባይም ሲሞላ ይወስደዋል ቤቱን
ወዳጅም ሲከዳ ያዞረዋል ፊቱን**

**አባይ ተቃጠለ ከነቀጤማው
አንቺን የሳመ ሰው ውሃም አይጠማው**

**አባይን በታንኳ ሲሻገሩ ባይ
በእግሬ ገባሁበት መከራየን ላይ**

**አባይን ተሻግሮ አባይ አለ ወይ
ሞትና መለየት አንድ አይደለም ወይ
ሞትና መለየት ምን አንድ አደረገው
ያው ሞቱ ይሻላል ቁርጡ የታወቀው**

**አብረን ተቀምጠን ያልጠገብኩሽን
እስቲ ተለያይተን እንየው ጉዱን**

**አብረን እየበላን ለምን ትሰርቂያለሽ
አትነግሪኝም ወይ ሌላ ሆድ እንዳለሽ**

**አብሬያት ተኝቼ ትንፋሿን ባጣው
ብርክርክ ብትንትን እቃ እንደጠፋው**

**አብሬያት እያለሁ የለሁም የለሁም
የነገረችኝን አንዱን አልሰማሁም**

**አብከንካኝ ይለኛል አብከንካኝለ እሱ
እያብከነከነኝ በአይንና በጥርሱ**

**አትሂድ በጨለማ ይደበድቡሃል
አንት ያገሬ ጀግና ባለ ደም ሆነሃል**

**አትሸበር ሆዴ አትበል ናድ ናድ
ወዶ መለየቱን አርገነዋል ልማድ**

አትበል ቀናሁ ቀናሁ ይሉሃል ተናዳጅ
የት ይገኛል ብለህ ሰው ያልነካው ወዳጅ

አትንኩት ራሴን ጭራሹን ያመዋል
አትንኩት አንገቴን ጭራሹን ያመዋል
ጥሩልኝ ያንን ልጅ ህመሜን ያውቀዋል

አትወደኝም ያልሺው የጠላሁሽ የታል
አንድ አንጀት ቢኖረኝ ተኝተሸበታል

አኡሬልሻለሁ ኩታ ለብቻው
አልደባልቀውም ፍቅርሽን ከሰው

አናግሩን በጥበብ ጭንቅ አንችልም እኛ
ፍቅር ሰላም እንበል በወሎ አማርኛ

አንለይ አንለይ አንለይ ስልሽ
የተለየን ለታ ምን አለ ሆድሽ?

አንለይ አንለይ እኛ ሁለታችን
ምስጢራችን ብዙ ነገረ ስራችን

አንበሳ ቢታሰር እደጃፍሽ ላይ
ዘንዶ ቢጠመጠም እወገብሽ ላይ
አንቺ ልከሽብኝ እቀራለሁ ወይ

አንበሳን በጡጫ ይለው የነበረ
ነብርን በቡጥጫ ይለው የነበረ
ልቤ አንቺ ጋር ሲደርስ ምነው ደነበረ

አንበሳ ጋማውን ቢያኩት ይደማል ወይ
የከፋው ሰው ሲሄድ ይሰናበታል ወይ?

አንተ ሰርገኛ ነህ እኔ ሃዘንተኛ
ላክልኝ ፎቶህን አቅፌው ልተኛ

አንተ አውራ ጎዳና ቀጭን መንገድ አውጣ
የምናፍቃት ልጅ በቶሎ እንድትመጣ

አንተ አገር ዘወር በል ያን አገር ልይበት
ትዝ አለኝ ደረቷ ሸጉጥ እምልበት


35

አንተው በገዛ እጅህ ሃይ ሃይ ብለኸኝ
ጭምቷን ወዳጅክን እብድ አደረከኝ

አንቺ ሆየ ለኔ የሚሿት ዘፈን
አምና ብር በላች ዘንድሮ ወይፈን

አንቺ ልጅ ቡናውን ደህና አርገሽ ቁይው
አንቺ አሮ ብታይው ውስጡ ጥሬ ነው

አንቺ ልጅ እቃሽን አትከታተችም ወይ
ከማሰረቅ ሌላ ስራ የለሽም ወይ?

አንቺም በዛ ሂጂ ወደ ፈረደብሽ
እኔም በዚህ በኩል ሰው አገኝሁብሽ

አንቺ ምን ታደርጊ እኔ አኮራሁሽ
ካልጠፋ ፍርንባ ልቤን ሰጥቼሽ

አንቺም እንዳትመጭ ታጠረ መንገዱ
እኔም እንዳልመጣ ክረምት ያህላል ጉዱ
ይሞክረኝ ጀመር ወደ ማሳበዱ

አንቺም እዛ ሆነሽ እኔን አንቀላፊ
እኔም እዚህ ሆኼ አንቺን ለአንቀላፋ
እንዲህ አይደለም ወይ መወክል ሲከፋ

አንቺ ስትተይው እኔ አልተወውም ወይ
የዛፍ እንኳን ጥላው ይዟዟር የለም ወይ

አንቺ በዚያ ብትሄጂ እኔም በዚህ ሄድኩኝ
ብድሬን ተወጣሁ ህመሜንም ዳንኩኝ

አንቺን መሳይ ቆንጆ እኔን መሳይ ልጅ
ኮከብሽ ኮከቤ ባይገጥም ነው እንጂ
ኮከብሽ ኮከቤ የገጠመ ለታ
ለሚካኤል ጃኖ ለጊዮርጊስ ኩታ

አንቺን አልኩኝ እንጂ ለልቤ ኩራቱ
ይወለድ የለም ወይ ሸጋ በየቤቱ

አንቺን አንቺን ብየ አንቺን ካላገኘሁ
እኔስ ሞቴን እንጂ ሌላም አልተመኘሁ

አንቺ አለሽኝ ብየ ጠልቼ ሁሉን
እንዴት ጦም አዳሪ ከርታታ ልሁን

አንቺ አታላይ ሆነሽ እኔ ተታላይ
እንዲህ ተፈራርተን ይዘለቃል ወይ?

አንቺ አታውቂም እንጂ ሽሽግ ያለ ኑሮ
ማን ያወጣሽ ነበር ከሆዴ በርብሮ

አንቺ አንጎራጓሪ የፍቅር አውድማ
ምነው ይኸን ሰሞን ድምፅሽ አይሰማ?

አንቺ እንደምን አለሽ እኔስ እንደ ምንም
እግዜር የሰጠውን ሰው አልችል አይልም

አንቺ እንደምን አለሽ እኔ እንዳለሁ አለሁ
የፍቅር መጫኛ አጋሰስ ሆኛለሁ

አንቺ እንደምን አለሽ እኔ እንዳለሁ አለሁ
ፍቅር ማንን ገድሎ እሞትልሻለሁ

አንቺ ከኔ በልጠሽ እኔ ካንች አንሼ
እንታረቃለን ብድሬን መልሼ

አንቺ ወዲያ ማዶ እኔ ወዲህ ማዶ
አንገናኝም ወይ ተራራው ተንዶ?

አንቺ የአዳል በግ ነሽ የትም ትለምጃለሽ
ለእኔ ምን መድሃኒት ትተይልኛለሽ?

አንቺየ ምንሽር መሆንሽ ነው ወይ
ስንት ሰው አለቀ በደረትሽ ላይ

አንቺ የአገሬ ልጅ መስታወቴ ጌጤ
ምን አድርጌሻለሁ ሳይሽ መደንገጤ?

አንቺ የጌታ ልጅ የምኔ የምኔ
ለሊት አላገኘሽ ቀን አይጥልሽ ከኔ

አንቺ የጥቁር ልጅ ዘረ ጠቆርቋራ
ክንፍ አወጣሁልሽ ልበር እንዳሞራ

አንቺ ጥቁር ድንጋይ ፍቅር አይገባሽ
እኔ ብረት ምጣድ ተቃጠልኩልሽ

አንቻሮ ቀረና ቃሉ ተገበየ
ቀረ ወዳጅ ሁሉ እንደተለያየ

አንች ልበ ደንቆሮ አንች ልበ ድንጋይ
ሰው ረግጦ ሄዶ ሰው ይገኛል ወይ?

አንች ቀጣፊ ዋሾ እኔም አወኩብሽ
ወይ ከሱ ወይ ከእኔ አይሆንም ወይ ልብሽ

አንዲት ምንጭ ነበረች እኛ እምንጠጣት
አንኮላ ገባና አደፈረሳት

አንድ ለአንድ መታገል ሲያቅተው ሰው ሁሉ
አንቺ ሰው በሰው ላይ ትጥያለሽ አሉ

አንድ ስኒ ቡና ለአመሌ በቂ ነው
ሱሰኛ ነው ካልሽኝ መደጋገሜ ነው

አንድ እንጀራ ለኔ መስታወቴ ነሽ
ሁልጊዜ የሰው ፊት ታሳይኛለሽ

አንድ ፈረስ ነበረኝ ዋ እንደኔ የከፋው
የሆዴን በአዋየው የጉንጩን ሳር ተፋው

አንጀቴ ተቆርጦ ስቀጥል ከርሜ
ደሞ ሰው ወደድኩኝ እርም የለኝም እኔ

አንጀቴ ተቆርጦ ከሆዴ ከወጣ
እንግዲህ ሃኪሙ ምን ሊቀጥል መጣ?

*አንጀቴና ሆዴ ተጣልተውብኝ*
*ተፋጠው ተናንቀው ሊጋደሉብኝ*
*አንተም ተው አንተም ተው ብየ እንዳልለው*
*ይኸም አንጀቴ ነው ይኸም ሆዴ ነው*

*አንጥፉ ልተኛ ወጉ ይድረሰኝ*
*ይመጣ የለም ወይ ሊቀሰቅሰኝ*

*አክርማ እንኳን የለኝ ሰፍቼ አልጨርሰው*
*እንዴት በያለበት ጅምር ይተዋል ሰው*

*አክ እንትፍ አክ እንትፍ ቅሪ እንደ ምራቁ*
*ከዛች ልጅ ወዲያ ቀርቷል መናፈቁ*

*አወይ ልጅነቴ ነፍስ አለማወቄ*
*ሲገረድፉልኝ አለመሰለቄ*

*አወይ ፈሪ ፈሪ አወይ ፈሪ ብልጡ*
*ሲሸሽ የሚያይበት አይን አለው በቂጡ*

*አውላላው ሜዳ ላይ ሽንጧ እያረገደ*
*እንኳን እኔ ባዳው ወንድሟም አበደ*

*አውላላው ሜዳ ላይ አዋልላኝ አዋልላኝ*
*ከነ አሽከሯ ሄደች ከነ አሽከሬ ገድላኝ*

*አውቄብሻለሁ ያንቺን ችላ ማለት*
*አውታታ ከርታታ አረኩት ለማለት*
*አውታታ ከርታታ ከወደደልሽ*
*እስቲ ልንከራተት ልዋትትልሽ*

አውቄ ነው እንጂ እንደው ስግደረደር
እኔስ ለወሎ ልጅ ውሃ ሽጬ ልደር

*አዙረህ አዙረህ አገሬ መልሰኝ*
*በሹም የታዘዘ አፈር አታልብሰኝ*

*አየ ጉድ አየ ጉድ አየ ጉድ እንግዲህ*
*ጆሮየ ከሰማ አይኔ ካየ ወዲህ*

አየ ጉድ አየ ጉድ ጉድ እስከ ወዲያኛው
የወደዱት ሲሞት የት ነው መገናኛው

አይላክብሽም ሀመሜም ቢጠና
ከሆዴ ወዲያ ሰው ማን ያውቅሻልና

አይሽ አይሽና ይመጣል እንባየ
አንቺም ወይ እድልሽ እኔም ወይ እጣየ

አይቆረቁረኝም ብተኛ መሬት
ከትዝታሽ ጋራ ስንጨዋወት

አይኔማ ወዳጅሽ ካለ አንቺ አላይ አለ
ጥርሴማ ወዳጅሽ ካለ አንቺ አልስቅ አለ
ጆሮየ ወዳጅሽ ካለ አንቺ አልሰማ አለ
ሆዴ ነው ጠላትሽ እህል በልቶ አደረ

አይንሽን አይኔ ላይ አርገሽው ቢሰበር
አሁን በማን ዳኛ ትከፈይኝ ነበር

አይንሽ ያምራል ብየ ተወራርጃለሁ
ጥርስሽ ያምራል ብየ ተወራርጃለሁ
ብቅ በይ ያገር ልጅ እረታብሻለሁ

አይንና ጥረሱንስ በጊዜ ሸኘነው
ሽንጡ ማደሪያ አጥቶ ሲጓዝ አገኘነው

አይንና ጥርሷማ መች ይበልጣል ከሰው
ከንፈሯ ነው እንጂ እህል ያልቀመሰው

አይከለከልም አይንና ወዳጅ
ባይሆን በአንድ አይበላም በአንድ አይጠጣም እንጂ

አይወዱ ወድጄ የጎረቤት ልጅ
ራቴን ስበላ ልቤ ወደ ደጅ

አይዞሽ ያገሬ ልጅ እመጣልሻለሁ
አልተደላደልኩም በአንድ እግሬ ቆሜያለሁ

አይደለሁ ሸረሪት አልገባ በዋልታ
ጭንቅ ነው ጥብ ነው ያለሽበት ቦታ


40

አዲሱን ሱሪየን እሳት ፈጀው ማታ
እቱ ያንቺን ነገር ስቋጥር ስፈታ

አዲስ ቤት ሰርቼ ክዳኑ ሲቀረኝ
በሽታየ መጣ አፍርስ አፍርስ አለኝ

አዲስ ቤት ተሰርቶ እለቱን አይሞቅም
ውልግድና ውልግድ አይነፋፈቅም

አዲስ አበባ ላይ መንታ ነው መንገዱ
አንዷ  ትቀራለች ወደ አንዷ ሲሄዱ

አዳል ግመሊቱን ይላታል ቢጨንቀኝ
አይገልም ወይ ፍቅር የከሳ ሰው ቢያገኝ

አዳራሹ ቆሜ እልፍኝ ስሚገት
አንቺን አንቺን ሳይ ነው የተረታሁት

አገሩ እሚኖር ሰው የገደል ግማሽ
እሰው አገር መሄድ ያደርጋል ትንሽ
ከትንሽም ትንሽ ያደርጋል ደንቆሮ
ውሻውን አልፌ ነከሰችኝ ዶሮ

አገሩ የንጉስ ነው ገንዘብ ነገ ያልቃል
ክፉ ነገር ከሆድ መች ይነቃነቃል

አገሩ ደጋ ነው ብዙ ሃብት አላት
እኔን ይዞ መብላት እንዴት አቃታት

አገሩ ጉራንጉር ስፍራው የወንበዴ
አሁን ስንቱን ዘሎ አንቺን አለ ሆዴ?

አገሩ ጉራንጉር ታቦት የሌለበት
ላኪልኝ ማተብሽን እኔ ልቁረብበት

አገራችን ታምማ ተኝታ በአልጋ ላይ
ጥለናት መጥተናል ሞት ሽረቷን ሳናይ

አገራችን ወሎ ስማችን ወሎየ
በነካኩንና ጉዳችን በታየ

አገሬን አገሬን አይልም ወይ ሰው
ክፉ ሲናገሩት ሆድ እየባሰው

አገሬን አገሬን የምትል ወፍ አለች
እኔን እኔን መስላኝ ታሳዝነኛለች

አገሬ አምባሰል ነው ያለችው ያቺ ሰው
ትዝታዋን እዚህ ምን አልከሰከሰው?

አገሬ አገሬ አትበል አንተ አገረ ብርቁ
እኛም አገር አለን የሚታይ በሩቁ

አገሬ ወልድያ አሳለም ወይ ያ ሰው
ትዝታውን እዚህ ምን አልከሰከሰው?

አገርሽ ባቲ ነው የለው መገናኛ
ይመጣል ትዝታሽ የልቤ መፅናኛ

አጉል ተጀምሮ ፍቅር ብሎ ጣጣ
የት ይደረስ ይሆን መለየት ሲመጣ?

አጎንብሼ ልሂድ እንደ ሰረቀ ሰው
ይኸ ቀና ማለት ቤቴን አፈረሰው

አጥሩ አልታጠረ አልጠፋ መንገዱ
ምን ያደርግልሻል በሰው ላይ መሄዱ

አጥርሽ ገረገራ ውሻሽ ተናካሽ
አርጊኝና ልሂድ ከመቀነትሽ
ምንድን ነው ቢሉሽም እጣን ነው ብለሽ
አጢሽው ቢሉሽም ገል የለም ብለሽ
ፍቅር እንዲህ ያልፋል አንቺ ካልለገምሽ

አጥቢያ ዳኛ እንዳትሄጂ እቃ ቢጠፋሽ
እዛው ከጎረቤት እኔው ነኝ ሌባሽ

እሄዳለሁ ባቲ በኮምቦልቻ በኩል
ጠይም ልጅ አይኔ ላይ ተሸክሜ እንደ ኩል

42

እሄዳለሁ ብየ ሰንቄን ሰንቄያለሁ
የእህል ውሃን ነገር እኔ ምን አውቃለሁ

እሄዳለሁ እንጂ ከመሄድ አልቀርም
ፍቅር ሲደራ እንጂ ሲፈርስ አይቸግርም

እሄድ እሄድና እላለሁ እረፉ
የጥርሷ ንቅሳት እየታየኝ ዘርፉ

እህህ ማለትን ማንም አያውቀው
ከሆዱ ውስጥ ገብቶ ካላስጨነቀው

እህህ ማለቷ መታመሟ እንጂ ነው
እስኪ ጠይቁልኝ ምኗን ነው ምኗን ነው

እህህን ለፈረስ ያስተማርኩ እኔ ነኝ
እሱ ጥሬ እያጣ እኔ እየቸገረኝ

እህህን በሆዴ ምን አበረከተው
ጥንቱኑ አለመንካት ከነኩ አለመተው

እህህ ጧት ማታ እህህ ለሊት
እይው ደመወዜን ካንች ያገኘሁት

እህህ ጧት ማታ እየየ ለሊት
ይኸ ሆኗል ትርፌ ካንቺ ያገኘሁት

እህሉን ብበላው ወዴት ይቀመጣል
አንድ አንጀት ቢኖረኝ ተኝተሸበታል

እላይኛው ግቢ ቆሜ ተሟግቼ
እታችኛው ግቢ ቆሜ ተሟግቼ
ያቺን ልጅ ወሰዷት ምስክር አጥቼ

እልም ጭልጥ ነው ውሃ አይለመጥም
ጠላት ወዳጅ ላይሆን አልለማመጥም

እልከው ሰው ባጣ እናገረው ባፍር
እተቀመጥኩበት ለፋሁ እንደጠፍር



43

እመንታ መንገድ ላይ ልቤ መንታ ሆኖ
መለያየት አይቀር ሰውና ሰው ሆኖ

እመጣለሁ ብሎ ሰው እንዴት ይዋሻል
ማበል እንኳን አንቺን መሬት ያበላሻል

እመጣለሁ እንጂ መንገዱን ጠይቄ
እስከ መቼ ድረስ እንዲህ ተጨንቄ

እመጣለሁ እያልሽ እየቀረሽብኝ
በሽታየ አንቺ ነሽ በሽታም የለብኝ

እምቢ ብላ ነበር እየኮበለለች
ባቲ ላይ ሳትደርስ ተገርፋ ተያዘች

እረኩም እረኩም ይሸታል ገላሽ
እንዲያውም በመላ የወሎ ልጅ ነሽ

እረ ይላል እንጂ ምስለኔ አይዋጋም
እንዴነሽ አገሬ የታጠርሽው በአጋም

እራቴን ከበላሁ ይኸው ስምንት ቀኔ
ምሳየን ከበላሁ ወር ካሰራ አምስት ቀኔ
እንደ አንቺ የጡር ሰው ርሃብ ቻይ እንደ እኔ

እርር ብግን በል እንግዲህ ቅመሰው
እግደረደር ብለህ አሳከፍከኝ ለሰው

እሱ አስታርቁኝ አይል እኔ አስታርቁኝ አልል ሁለታችን ኩሩ
እባካችሁ ሰዎች የዛሬን ሽምግሉ
አየሁት ተቀጣሁ ቀረ አመሌ ሁሉ

እሳቱን አንድዱት አልወድም ጨለማ
የዚህ አገር ልጅ ነኝ የዚህ የከተማ

እሳት መሬት ቢነድ አይደርስም ሰማይ
ላይጨርሱ ፍቅር ይጀመራል ወይ?

እሳት እሳት አለኝ አይኔን ብዳብሰው
መሄጃ መውረጃ እንደምን ያጣል ሰው

እሳት ከነደደ መች ይገዳል አመድ
እንዴት ነው ሰው ሁሉ አጥፊውን የሚወድ

እስላም አረደው ክርስቲያን አረደው ጨጓራና ጉበት
ያም ስጋ ያም ስጋ በላሁ ምን አለበት

እስላም ክርስቲያኑን አደባልቄው
ዛሬ ደስ ይበለኝ ነገ ቄስ ይፍታው

እስከ ዛሬ ድረስ የስጋ ጣእም ሳላውቅ
እንዴት ይጣፍጣል ታናሽና ታላቅ

እስኪ ልነሳና ላቃጥለው ቤቱን
ማደሪያ ሲጨንቀው ይመጣ እንደሆን

እስኪ ልነሳና ልበለው እየየ
ቀን ሲጫወት ውሎ ማታ ስተለየ

እስኪ ልነሳና ድምፄን ላሰማው
እሱንም እንደ እኔ ግራ እንዲገባው

እስኪ መላ ምቺ መላ ከአንቺ ይገኛል
እኔማ ወድጄሽ ይደናገረኛል

አስኪ በስመአብ ብየ ልጀምር ሰላምታ
ለተቀመጥሽበት ለአለሽበት ቦታ

እስኪ እናንተ ሂዱ የኛም ወደዚያው ነው
የፍቅር መንገዱ ፊትና ኋላ ነው

እስኪ እናንተ ብሉ የኔ ራት ገና ነው
ይፈጫል ይቦካል ባለ መከራ ነው

እስኪ እናንተ ተኙ እኛ ስራ አለብን
ግንብ እንገነባለን ፍቅር ተንዶብን

እስኪ እናንተ ተኙ እኔ እቀመጣለሁ
አይኑ ሲሙለጨለጭ ትቼው መጥቻለሁ


45

እስኪ እንደ በርበሬ ላይ ላዩን ላምሰው
ሲያቀብጠኝ ወድጄ ይፋ እማይወጣ ሰው

እስኪ እንደ ጎጃሞች አንደዜ ምችና
ውሰጅው ማተቤን ከአንገቴ ፍቺና

እስኪ እንደ ጎጃሞች እንዳየን እንዳየን
ነጭ ጤፍ እንብላ ዘንጋዳው ይቆየን

እስኪ ውሃ ስጡኝ አፌን ልጉመጥመጠው
የዛችን ልጅ ከሰው እንዳልደባልቀው

እስኪ ዘራፍ በሉ ዘራፍ ለአፍ ይሞቃል
የጀግኖቹማ አገር ከሰማይ ይርቃል

እስኪ ዝም በሉ ሰው ይነጋገራል
መናፈቄን አውቃ መጥታልኝ ይሆናል

እስኪ ዶማ ስጡኝ ምኼ እቀበርበት
እንኳን በሰው አመል በራሴ አላውቅበት

እስኪ ጎጃም ሄጄ ልጠይቅ አቡን
የዛችን ልጅ ነገር መጨረሻውን

እስኪ ጠይቁልኝ መቼ ነው ቅዳሜ
የተቀላቀለው ደምሽና ደሜ

እስኪ ጠይቁልኝ ሚስቲቱን በሰው
ባሏ ልቤን ወስዶ የት አደረሰው

እስኪ ጠይቁልኝ ምንድን ነው ነገሩ
እንደ ነፍሰ ገዳይ የጠፋው ካገሩ

እስኪ ጠይቁልኝ አጋፋሪውን
ጠጅ አለብርሌ ይጠጣ እንደሆን

እስከታም እንዳልወርድ አይችልም ጉልበቴ
እንዳው ወረድ ወረድ የሰራ አከላቴ

እስክትመጭ ድረስ እስካይሽ ብቸኩል
ፊቴን ዞሬ ተኛሁ ባለሽበት በኩል

እሷን ያጣሁ ለታ ተጋድሜ በአልጋ
በእህህ ብቻ ነው ለሊቱ የሚነጋ

እሷ ጥሬ አትበላ እህል አልቀምስ እኔ
ልንካረማት ነው ያች አህያና እኔ


እሺም እንዳልለው የባልንጀራየ
እምቢም እንዳልለው ወደደው ገላይ
እስኪ ይሁን በአቦ አይለፍ ለሌላ
ምን ይመጣብኛል ከወየጉድ ሌላ

እሾህ ብቻ ሆነ እግሬን ብዳብሰው
እንዴት መራመጃ መሄጃ ያጣል ሰው

እበላለሁ እንጂ በጦም በሁዳዴ
እንግዲህ አይሳሳም ለአንቺ ሸሮ ሆዴ

እበላስ አልበላስ ሆዴን ማን ጠየቀው
ያው እሱ ነበረ ርሃቤን የሚያውቀው

እባብ ከድንጋይ ስር በእጅ አይመዘዝም
የዘንድሮስ ፍቅር እንደው ዝም እንደው ዝም

እባቡሩ መንገድ የቆምኩት አሁን
ስንቱን አሳልፌ እዘልቀው ይሆን

እባካችሁ ሰዎች እንግባ አገራችን
እንደ ወጡ ቀሩ አይበል ጠላታችን

እባካችሁ ተውኝ እንደራስ ነው ፍርድ
ጭምት ያሳብዳል ዛርና መውደድ

እባክህ ቁልቁለት ተወኝ አታዳፋኝ
ወዳጄን ሸኝቼ ቆሜያለሁ ቢከፋኘኝ

እባክህ አሞራ ላፍስልህ ጥሬ
ትነግረኝ እንደሆን የዛችን ልጅ ወሬ

እባክህ አሞራ ና ተላከኝና
አንተ የሰው ጣራ ትደፍራለህና
ብታገኝ ንገራት ብታጣት ቶሎ ና
ዋ ብሎ መመለስ በአንተ ያምራልና

እባክህ አሞራ አቀብለኝ ወሬ
አቃጠሉት መሰል ሸተተኝ አገሬ

እባክሽ አሞራ ጠይቀሽው ነይ
እኔ አጣሁ አምሳያ እሱ አገኘ ወይ?

እባክሽ እናቴ በጣባ ወተት
ያንን ቀበጥባጣ አባብልበት

እቤት እገባና አለቃቅሳለሁ
እደጅ እወጣና አለቃቅሳለሁ
አንቺንም አይኔንም አጥቼው አርፋለሁ

እተውሽ እልና እጠላሽ እልና
ይመጣል አንገትሽ ማተቡን ያስርና

እቱቱ በረደኝ ቀዘቀዘ ቤቱ
አስለምዶኝ ነበር ሸጌ በደረቱ

እቱቱ በረደኝ ብርድ ይሞቃል ወይ
አቅፈው ያልሳሙት ሰው ይናፍቃል ወይ?

እቱቱ በረደኝ ብርድ ይሞቃል ወይ
የማያውቁት አገር ይናፍቃል ወይ?

እቱ እንደምን አለሽ እኔስ እንደምንም
እግዜር የሰጠውን ሰው አልችል አይልም

እቱ እንደምን አለሽ እኔ እንዳለሁ አለሁ
የፍቅር መጋዣ አጋሰስ ሆኛለሁ

እቱ እንደምን አለሽ እንደምን ከርመሻል
አመመሽ ደከመሽ ዋ እንደ እኔ ሆነሻል

እቱ የአንቺ ነገር ከኮሶ ባሰሳ
ያስቀምጠኝ ጀመር ሌሊት እያስነሳ

እቲቱ ባንቺ ቤት ብዙ ተለመደ
አንቱ የሚል ጠፋ ሁሉ አንቺን ወደደ

እኒህ አምባሰሎች አበላል ያውቃሉ
በገብስ እንጀራ ላይ ሳማ አርጉ ይላሉ

እናቲቱ ናቸው የኔ ደመኛየ
እሷማ ምን አለች ማሬ ወለላየ

እናትህን አትውደድ ለዘጠኝ ወር እድሜ
እኔ አርግዤሃለሁ እስከ ዘላለሜ

እናትህ ይሉኛል እረ ልጄ ልጄ
አባትህ ይሉኛል እረ ልጄ ልጄ
እስኪ ትውልድህን ቆጥረህ ንገረኝ
ከወንድም አንተ ነህ ትዝ የምትለኝ

እናትና አባትሽ ምንኛ ተጎዱ
ዘጠኝ ወር አርግዘው ሻፋዳ ወለዱ

እናትና አባትሽ ስጋ ነው እርማቸው
አንጀት ትበያለሽ አንቺማ ልጃቸው

እናትና አባትሽ በፍቅር አረጁ
ምነው በኛ ጊዜ ሰንሰለት አበጁ

እናትና አባትሽ አይወዱም እንግዳ
ሳሚኝና ልሂድ በሳንቃው ቀዳዳ

እናቷ ምሳዋን አልሰጧትም ወይ
ምን አይነቷ ልጅ ናት እህል እህል ባይ

እናንተ እራት ብሉ የኛ እራት ገና ነው
ይፈጫል ይቦካል ባለ መከራ ነው

እኔ ለስንታችሁ ዋትቼ ልሙት
ያውላችሁ ልቤ ተቀራመቱት

እኔ ለአንቺ ብየ ብከሳ ብነጣ
ኮሶ ታየው አለኝ ሰው ነገር አያጣ

እኔ ለአገሬ ልጅ ለወንዜ ልጅማ
አፌም አይናገር ድምፄም አይሰማ

እኔ መች አልኩና የጌታ ልጅ ወዳጅ
ብጤየን አልኩ እንጂ ሲያመኝ እሳት አንዳጅ

እኔ መንገደኛ ስንቁ የተቦካ
አንጫወትም ወይ እስኪጋገር እንኳ

እኔም ለፈለፍኩኝ መላ አገሩ ሰማ
ግደይኝ አንቺ ልጅ ከተጠቀምሽማ

እኔም ልጅ እሷም ልጅ ተጋቡ ይሉናል
የተሰቀለውን ማን ያወርድልናል?

እኔ ምን አውቃለሁ ጉዳይ እንዳላት
ውላ ውላ መጣች ከማልወደው ቤት

እኔ ምን ቸገረኝ ቢፈርስ አዳራሹ
ይቁምልኝ እንጂ የአንድ ሰው ትንፋሹ

እኔስ መስሎኝ ነበር የተገናኘን ለት
ለካስ ለመከራ አሳር ለመሸመት
ምነው በቀረብኝ የዚያን ለት የዚያን ለት

እኔስ ብየሽ ነበር የአይኔ ጉድፍ አውጭ
እንዲህ ወደ ኋላ ነገር ልታመጭ

እኔስ አንቺን አንቺን ሸተተ ገላየ
ተሰራጨሽብኝ በሁለንተናየ

እኔስ አንቺን አንቺን የልጅነቴን
ፍቅር እንደ ሀሁ ያስቆጠርሽኝን

እኔስ እሄዳለሁ እግሬ እስከቻለልኝ
መቼ እጠብቃለሁ በቅሎ እስኪጫንልኝ

እኔስ እሄዳለሁ ከመሄድ አልቀርም
ፍቅር ሲደራ እንጂ ሲፈርስ አይቸግርም

እኔስ ከወሎ ልጅ አንዱ ከደረሰኝ
አጠረ ቀጠነ አልልም አነሰኝ

እኔ በአንቺ ነገር ምን ያልሆንኩት አለኝ
እየተመሰለ ጉቶ እንኳን ሲያሞኘኝ

እኔና አንቺ ሆነን በሰራነው ነገር
ይፈጫል ይቦካል ይታመሳል አገር

እኔና አንቺ ብቻ ርሃብ አይደፍረን
ፍቅር ብቻ ሆኖ ራት ምሳችን

እኔና አንቺ ደህና ግድ የለም ግድ የለም
ድህነታችንን የሚቀማን የለም

እኔን አዲስአባ ካረገኝ ከራሚ
አንቺን ድሬደዋ ካረገሽ ከራሚ
ደብዳቤ ላኪልኝ ለልቤ አስታማሚ

እኔ አላቅም እንጂ ጥዶ መጋገር
አንቺስ እህል እህል ብለሽኝ ነበር

እኔ አንቺን ስወድሽ አለኝ አማርኛ
ቀኑን አልቀመጥ ለሊቱን አልተኛ

እኔ አንቺን አይደለሁ በፍቅር አልለግም
አሞኝ አሞኝ ውሎ መጣሁኝ ሳዘግም

እኔ እንደ ቡሃቃ እየበላሁ ነጣሁ
ወዳንች እምልከው እማምነው እያጣሁ

እኔ እወድሻለሁ ያንቺ መውደድ የታል
አይንሽ እንደ እረኛ ከብት ይመለከታል

እኔ እየተከተልኩ እሷ እየመራችኝ
ስማዳ ስማዳ ስማዳ አገባችኝ

እኔ እየወደድኳት እሷ እየጠላችኝ
ዛሬስ ይብላው ብላ ጅብ አስራ ቆየችኝ

እኔውም እብድ ነኝ እወቁኝ አበዛሁ
የት ሆኜ ልበላው አዲስ መሬት ገዛሁ

እኔውም እብድ ነኝ ውቃቢ የራቀኝ
ከሄደ ኋላ ነው ሰው የሚናፍቀኝ

እኔው በገዛ እጄ ለፍቅር ሟች ብሆን
አጠፋ ይቀጣ የሚለኝ ማን ይሆን

እኔው ተውኩሽ እንጂ ማን አባቱ ቀማኝ
ሰጠሁሽ ለድሃ ለባሰበት ለማኝ

እኔ ዘመድ የለኝ ንፋስ ነው ዘመዴ
ትንፋሿን አምጥቶ ከተተው ከሆዴ

እኔ ዘመድ የለኝ አንቺ ዘመደ ብዙ
አስቀሩሽ መሰለኝ ምክር እያበዙ

እኔ የልጅዋ ልጅ እሷ የእናቴ እናት
አኳኋኗ ሁሉ እንደ አያት እንደ አያት

እኔ ግልገል በቅሎ ከበለገ እምግጥ
ባለ ብዙ ንብረት ባለ ሃብት ይደንግጥ

እንስፍስፌ ቢሄድ እንስፍስፌ መጣ
እኔም እንስፍስፍ ነኝ እንስፍስፍ አላጣ

እንባየን በዋንጫ ልቤን በሙዳይ
ልኬልሽ ነበረ አገኘሽው ወይ?

እንቅልፌም ውሰደኝ ጎኔም አርፈህ ተኛ
አልተገናኘንም እንግዲህ ዳግመኛ

እንተኛ ካላችሁ እንንገንደሰው
መኝታ እንደሆነ ቀርቷል ከአንድ ሰው

እንካ ትዝታህን ቆጥረህ ተረከበኝ
ፍቅርህ እንዲህ ይዞ ከሚያብከነክነኝ

እንክት እንክት አለ ጉልበቴ ሊሰበር
አወዳደቄ እንኳን ከቆንጆ ልጅ ነበር

እንክትክት አለና ተሰበረ ጎኔ
ወትሮም አወዳደቅ መኝታ አላውቅ እኔ

እንክትክት ያድርገው ያንን መስታወትሽን
እያየሽው ኮራሽ አይንና ጥርስሽን

እንኳን አንቺ ሄደሽ አሳይተሽኝ
ወትሮውም ልጅየው መንገደኛ ነኝ

እንኳን እንጉርጉሮ ስንት ያውቃል አምባሰል
በሆድ ብዙ ችሎ ያልተከፉ መምሰል

እንኳን ካገሩ ልጅ እንኳን ከእኩያው
ከማንስ ከማንስ ያብድ የለም ወይ ሰው

እንኳን ያንቺ ፍቅር ተጨምሮበት
ድሮም ሞቃት ነበር ሰኔና ግንቦት

እንኳን ያንቺ ፍቅር የትላንትናው
ድልድዩ እንኳን ፈርሷል ሚናስ የሰራው

እንዋደድ ነበር በልቶ እንደመጠጣት
ይኸው ተለያየን ደስ ይበለው ማጣት

እንደምነው አይንሽ ጥቁርና ነጩ
እንደ ባለስልጣን ፈላጩ ቆራጩ

እንደምነው ደሴ ወገብ ለወገቡ
እንዴት ነው አምባሰል ወገብ ለወገቡ
እንደምነው ባቲ ወገብ ለወገቡ
የእነ ቆንጂት አገር የነአይጠገቡ



53

እንደ ባቲ መንገድ እንደ ቁልቁለቱ
ይህን ያክል ነው ወይ የፍቅርሽ ጥናቱ

እንደነ ራስ አሊ ሆ ሆ ልበልሽ
ብሎሽ እንደሁ ለኔ መቼም አላጣሽ

እንደ አላሻ ሜዳ ለጥ ያለው አመልሽ
ቁጭ በይ እናውጋ እንተኛም አልልሽ

እንደ አይን እንደ ጆሮ እንደ እግር እንደ እጅ
ወዳጅ ማለት አብሮ ሲማስን ነው እንጂ

እንደ እኔ ማን አለ ያልታደለ ሰው
ጨርሶ እንደ መብላት ጀምሮ ለሰው

እንደ እየሩሳሌም እንደ አክሱም ፅዮን
ተሳልሜው ልምጣ አይንና ጥርሷን

እንደ እየሩስአሌም እንደ ወዲያኛው
በአመት አንድ ቀን ነው የምትገኝው

እንደው ለልማዱ ጋደም ይላል ጎኔ
እንደው ለልማዱ ከደን ይላል አይኔ
ምን መኘታ አለና አንቺ ቀርተሽ ለእኔ

እንደው እልሻለሁ ዘመዴ ዘመዴ
እንዳልተወለድሽኝ እያወቀው ሆዴ

እንደ ጅሩ መንገድ ለጥ ያለው ወገቧ
በምን ያስታውቃል መራቧ መጥገቧ

እንደ ዛሬው ቢሆን ነፍስ እንደማወቄ
ማረኝ እለው ነበር እግሩ ላይ ወድቄ

እንደ ግልገል በቅሎ በራሴ ለገምኩኝ
ሰው መላኬን ትቼ እኔው ባዘገምኩኝ

እንዲህም እንዲህም እንዲህም አረገኝ
እኔ ከሱ ሌላ መድሃኒት ለአላገኝ

እንዲህ ነው ወይ ለካ የተመከረው
እኛም እናውቃለን ጣል አርጎ መተው

እንዲህ ዘንቦ ዘንቦ የደረቀ እንደሆን
እንዴት ያሉ በሮች ይጠመዱ ይሆን?

እንዲህ የሚያስከፋ ምን ተናገርኩት
ያንን ጋራ ዙረህ ተመለስ በሉት

እንዲህ ያለ ነገር የጠፋ ለመላ
እንዴት ይለያያል ሰው ሳይጠላላ?

እንዳላምሰውም አለ አባቱ ስንዴ
እንዳላሰጣውም ይታይ ሆነ ጉዴ
ስራይ ሆኖ ቀረ የሰው ሰው በሆዴ

እንዳብከነከንሽኝ እንዲህ በፈገግታ
አንቺን አያድርገኝ ያገኘሁሽ ለታ

እንዴት ያዘው ያዘው እንዴት ጣለው ጣለው
ይቸግር የለም ወይ ደም መላሽ እንዳለው

እንዴት ይጣፍጣል የሰው ቤት እንጀራ
በእሁድ በቅዳሜ በበአል የተሰራ

እንዴነህ በሉልኝ ያን የወዲያኛውን
ሲርበኝ ሲጠማኝ ሲያምረኝ የቀረውን

እንዴነህ እንዴነሽ አንባባልም ወይ
ሰው ከአባቱ ገዳይ ይታረቅ የለም ወይ?

እንዴነሽ አይባል ሰው በሰው መሃከል
ሂጂ አይቻት መጣሁ አይን አይከለከል

እንዴነሽ ውጫሌ እንደምነሽ ጢሳ
የተቋደስንብሽ ፍቅር ራት ምሳ

እንዴነሽ እንዴነሽ እንዴነሽ አሁንም
ያለሸበት ሰፍራ አያስተማምንም

እንጀራ ሆነና የሰው ቁም ነገሩ
አልቀመጥ አለ የሰው ልጅ በአገሩ

እንግዲህ ለባዳ እንግዲህ ለሰው
አፌም አይናገር ልቤም አይረሳው

እንግዲህ ለፍቅር ቤት አልሰራለትም
እየተጀመረ እየቀረ የትም



እንግዲህ እርም ነው ዱላ ላላነሳ
ሴትን በሴት መምታት ያከሳታል እሳ

እንግዲህ እርም ነው ጠይም ሰው አልወድም
በበረደው ሆዴ እሳት አላነድም

እንግዲህ ጀመረ ሆዴ ሊርበተበት
አራስም ልጅ ያድጋል እናቱ ሞታበት

እንግዳ በሽታ ታምሜ ባላቅ ነው
እባክሽ ንገሪኝ ሆድ ሲቆርጥ እንዴት ነው?

እንጠጣ ነበር ውሃ በአንድ ኮዳ
እጅግ ያሳዝናል ያመኑት ሲከዳ

እንጦጦም አልወጣ ዝቋላም አልወርድ
እዚህ ባታም አለች የምትወደድ

እኛ ምን ቸገረን መደሰት ብቻ ነው
የከፋው ስመጣ በሩን ማሳየት ነው

እኛስ በልተነዋል እሸት እሸቱን
እንግዲህ ለቃርሚያው ስደዱት ከብቱን

እኛ በአንገባበት ባይኖረን ጉዳይ
ያስ ማዶ ያስ ማዶ የኛ አይደለም ወይ?

እኛውና መጡ ደረሱ እዛ ማዶ
እየሸሹላቸው መከተል ተለምዶ

እወድሽ እልና ክፋትሽን ሳስበው
ይበተናል ልቤ የተሰበሰበው

እዘጋዋለሁኝ በሬን እንደ አመሉ
የት ሄደ ቢሏችሁ ከፍቶት ሄደ በሉ

እዚህ መጥተሽ በላሽ እዛም ሄደሽ በላሽ
ሰው ታዘበሽ እንጂ ሆድሽን አልሞላሽ

እዛ ማዶ ሆነሽ እዚህ የታየሽኝ
ስንቱን ጋራ ዙሮ ይመጣ ብለሽኝ

እዛ ማዶ ሆነሽ የምትታይኝ
እንድመጣ ነው ወይ ጅብ እንዲበላኝ

እዛ ማዶ ጭቃ እዚህ ማዶ ጭቃ
የዛች ልጅ ጫማ ዳር ዳሩ ጨረቃ

እዛም እዛም አትበል እንደ ቆዳ ገድጋጅ
እግዜር ከባረከው ይበቃል አንድ ወዳጅ

እዛም እዛም ያልኩት ሆዳምነቴ ነው
አንጀቴን አጥፌ በጠበኩሽ ምነው

እዝችም እዛችም መላላስ ከመጣ
እኔም ወጣ ብየ ላጥ አርጌ ልምጣ

እዝችም እዛችም ትወጋጋኛለች
እስኪ ዋግምት አምጡ በደም ትወጣለች

እየአቅበጠበጠኝ ቅጡን እያጣሁት
ልሰናበትሽ ነው ዛሬስ የመጣሁት

እየነካካሽኝ አታጠውልጊኝ
ወይ ቅጠፊኝና ደርቄ ልገኝ

እየየም አትበሉ እንዲያው ቅበሩኝ
ሳውቀው ገብቻለሁ ዘመድ ሲመክረኝ

እያዩ ነው መብላት እየተነተኑ
በየደረሱበት ልብ ሳይበትኑ

እይው ተመልከቺው የጉልበቴን ቁስል
ስድህ ያደርኩበት አንቺን ስል አንቺን ስል

እደጅሽ ይቅበሩኝ በስንደዶ ምሰው
እንዳይቆረቁረኝ አንቺን አንተርሰው

እድሌ ነው እንጂ ሌላ ምን አነሰኝ
ብርቱካን ሲታደል ሎሚ የደረሰኝ

እግሬን ሰባብሬ ልሰልቅ አጥንቱን
ካልሆነ ቦታ ላይ ማን ግባ አለው ጥንቱን

እግዚአብሄር ይመስገን ለሰው እጅ አልነሳም
እንደ መናፈቄ ደህና ነኝ አልከሳም

እግዚአብሄር ይማርሽ ከያዘሽ በሽታ
ትመጭ የለም ወይ የለቀቀሽ ለታ

እግዚአብሄር ይይልሽ አንድ አምላክ ጭምር
አስቀርተሽዋል ፍቅሬን በጅምር

እጥፍጥፍ ያለች ልጅ እንደ እባብ ሬሳ
ስትመጣ አትጠገብ ስትሄድ አትረሳ

እጦሳ ጋራ ላይ ጀንበሩ ጠለቀ
ምንም መላ የለው የጁን የለቀቀ

ኧረ ሆዴ ሆዴ ሆዴ ምን ትላለህ
ከአለው ልመድ እንጂ ከቀረው ምን አለህ

ኧረ ለመሆኑ የአንተ አንጀት እንዴት ነው
የእኔስ እምቢ ብሏል በአሰረው ብገንዘው

ኧረ ሰው አለቀ ሰው አለቀ በሷት
እሷ እየወደደ ለሚያመው ግድ የላት

ኧረ በላሞችሽ በነ ቀንደ ቦራ
እሾህ ወጋኝ ብለሽ ቅሪ ወደ ኋላ

ኧረ ባቲ ባቲ ባቲ ገንደላዩ
ሃድራው የሚገባው ደራርበው ሲተኙ

ኧረ ባቲ ባቲ ባቲ ገንደላዩ
ይመሻል ይነጋል ጠይም ልጅ እያዩ

ኧረ ተወኝ ልቤ ደርሶ መደንገጡን
ሞት አይቀርም ብየ ነግሬህ እርግጡን

ኧረ ተውኝ ተውኝ ተውኝ እባካችሁ
እንኳን የሞሰቡን የእጄን ተውኩላችሁ

ኧረ ተይ እረ ተይ እረ ተይ አይሆንም
ተኝቶ ሰው መግደል አያስመሰግንም

ኧረ ነይ ኧረ ነይ ኧረ ነይ ዝምብለሽ
አየ ጉድ ነው እንጂ ምን ይመጣ ብለሽ

ኧረ አብስሎ በላኝ ክፉ ነው ውሻችሁ
አታስጥሉኝም ወይ ያላችሁ ያላችሁ

ኧረ እንደምን አለሽ ለውሉ ለአዳሩ
ሞቀሽ ወይ በረደሽ ይኸ ቤት ትዳሩ

ኧረ የጁ የጁ ውድ ነን ውድ ነን
እህል እየበሉ ሰው ወዶ መመንመን

ኧረ ደሴ ደሴ እረ ቃሉ ቃሉ
ተናገረች መሰል እስኪ ብቅ በሉ

ኧረ ደሴ ደሴ ኧረ ቃሉ ቃሉ
እንደዋለ ቀረ ያ ቁምነገር ሁሉ

ኧረ ደሴ ደሴ ገራዶ ቢለን
የስንቱ መወክል ለከፈኝ እኔን

ኧረ ደሴ ደሴ ገራዶ ገራዶ
አለቀልሽ ልቤ ተንዶ ተንዶ

ኧረ ገርፋ ገርፋ ባቲ ከተማው
ከሚበላ በቀር የሚጣል የለው

ኧረ ጎንደር ግንደር እኔን ጎንደር ያርገኝ
የበሉት ሲስማማ የፈለጉት ሲገኝ

ኧረ ጀግናስ ይሙት ፈሪ ይኑር ቢሻው
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው

ኧረ ጠይም ጠይም ጠይም አሳ መሳይ
እኔ እናቷን ብሆን ለሰውም አላሳይ
ቁጭ ብየ እበላለሁ የሰጠኝን ሲሳይ

ኧረ ጠይም ጠይም ጠይም አትውደዱ
ጠይም ወድጄ ነው የጠፋኝ መንገዱ

## ከ

ከሁሉም ከሁሉም አይንህ ይሻለኛል
ምንም ሰው ቢበዛ አሻግሮ ያየኛል

ከሆዴ ተቀምጦ ናፍቆቱ ጎዳኝ
በእጄ እንዳልዳስሰው በአይኔ አይታየኝ

ከመሸ መጣና ተመልሶ ሄደ
እንደተጠላ ሰው እንዳልተወደደ

ከመንታው መንገድ ላይ ልቤ መንታ ሆኖ
መለያየት አይቀር ሰውና ሰው ሆኖ

ከበሽተኛ ቤት ወስደው ጥለውኝ
እሷም አልተሻላት እኔም ባሰብኝ

ከበሽታው አገር አባይ ጨፌ አድረን
እሷ ደህና መጣች አመመኝ እኔን

ከቤትሽ መጥቼ ቆሜ ከደጅሽ
ናፍቆኝ የነበረው ሞቀኝ ትንፋሽሽ

ከብት ጠፋኝ አለች ከቤቴ በላይ
እኔን መፈለጊያ ማድረጓ ነው ወይ?

ከሰብል መሃከል አግዳ ብዙ ሳም
ምን አይነቷ ልጅ ናት እህል አታስበላም

ከአለ አንድ ሰው አትጭን በቅሎዋ አመለኛ
እኛ ሳንጣላ አጣን መገናኛ

ከአልቸገረኝ መንገድ በደጅሽ አልፌ
ልቤን ትቼ መጣሁ ሳምባየን ታቅፌ

ከአልጋው ስንዝር የማታራርቀው
እንደ ባህር አረብ ቅስሟ የደመቀው
እንደ ቀትር እባብ ሽንጧ የረቀቀው
እንደ እየየሳሌም አንጀቷ የራቀው
ስትተኛ ክናዷ ስንዝር የምትርቀው
ስታንተርስ ክንዷን የምታስጨንቀው
ስትስም ከመሬት የምትደባልቀው
ትንፋሿ እንደ አረቄ ሃሞት የሚከተው
ከንፈሯ እንደ አራስ ልጅ የሚርበተበተው
እጥር ምጥን ያለች የልጅ እመቤት
ዘሯ የተጣራ ልቅም እንደ ስንዴ ጥሩ እንደ ወተት
የወሎ ሳዱላ መኳንንት ያጫት
ዳኛው ገሰገሰ ሊያፈጣጥማት
አጥንቴ ረገፈ ስሰናበታት
አትለማም አትሰማም እኔ እዚህ ስሞት

ከአባይ ወዲያ ማዶ ሸንብራ ዘርቼ
ወፎች ጠረጠሩት መሻገሪያ አጥቼ

ከአባይ ወዲያ ማዶ ትዝ የምትለኝ
እንድመጣ ነው ወይ ጅብ እንዲበላኝ?

ከአባይ ወዲያ ማዶ ዘመድ አለኝ ማለት
ዋ ብሎ መቅረት ነው ውሃ የሞላ ለት

ከአባይ ወዲያ ማዶ ያለችው እንዶድ
እንዴት አርገው ቢያጥቡት ይለቃል መውደድ

ከአንተ ከተለየሁ እስካሁን ድረስ
ወንዱ ሴት መሰለኝ እረግ አያድርስ

ከአንተ ከተለየሁ ይኸው ነው ስራየ
እንደ ገደል ውሃ ይፈሳል እንባየ

ከአንቺ ከተለየሁ የምበላው እህል
እንዳልሞት እንዳልሸር ይቺን ይቺን ታህል

ከአገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ
ቢጭኑት አህያ ቢቀመጡት ፈረስ

ከአገሬ ወጥቼ እሰው አገር ነኝ
እጅግም አልከፋኝ ደስም አላለኝ

ከእንጀራው አልበላ ከውሃው አልጠጣ
ቁርስ ራት ምሳየ አሷ እስክትመጣ

ከእንግዲህስ ወዲያ ብሞት ምን አለበት
ሳጣሽ ያዝናል ሆዴ ሳይሽ አላውቅበት

ከእንግዲህስ ፍቅር እርም ብየ ብተው
አይኔ መሰከረ ቅሌት አይታክተው

ከእንግዲህ አልበላም ብርቱካኔን ልጨ
መለየትን ያህል ከጎኔ  አስቀምጨ

ከእኛ ወዲህ እንጂ ከእኛ ወዲያ ሰው
በይ ሂደሽ በይ ሂደሽ በይ ሂደሽ እይው

ከአውሳሳው ሜዳ ላይ አውሳሳኝ አውሳሳኝ
ሄደች ከነአሸከሯ ከነአሸከሬ ገድላኝ

ከኮምበልቻ በላይ ከደሴ በታች
ቦርከና አፋፉ ላይ ያገኘናት ልጅ
በእጅ አትንኩኝ አለች በከንፈር ብቻ እንጂ

ከዛፉ ላይ ወጣሁ ከጠይሙ ላይ
ማን ያወርደኝ ይሆን እንግዲህ ዋይ ዋይ

ከዛፍ ላይ ወድቄ ከጠይም እንጨት
እጅ እግሬ ደህና ነው ልቤን አጣሁት

ከደጅሽ ልታረድ እንደ ጭዳ ዶሮ
የአንቺ ደመ ግቡ ሆኛለሁ ዘንድሮ

ከጓሮዋ ቆሜ ባነጥስ ባነጥስ
ወይ እሷ  ብቅ አትል ወይ ጥጃው አይበጥስ

ከፊት ከፊት አርጉት ትግባ በመንገዱ
ይቺን የወሎ ልጅ ጥላችሁ አትሂዱ

ከፋሽ ወይ ደስ አለሽ ስታጭኝ ካገሩ
ፍቅር ይከፈላል ከዋሉ ካደሩ

ኩታየን አንጥፌ ልተኛ ደጅህ
ከቤት እንዳልገባ አንተ እምነት የለህ

ካልተቀጠቀጠ አይበላም ቋንጣ
የዋግ ሹሞች አገር እንዴት ነው ሰቆጣ

ክትክታና ወይራ ሲማግዱ አይቼ
ሳገላብጥ አደርኩ የሰው ግንድ አምጥቼ

ክፉ ቢናገሩኝ ክፉም አልናገር
አገሬ እስክገባ ወንዟን እስክሻገር

ክፉ ተናግሬ ሆድም አላስብስሽ
የወሰደሽ ውሃ አውቆ እስኪመልስሽ

## ወ

ወረባቦ ግሸን ተንታና መቅደላ
እስኪ ለዛች ቆንጆ ስም አውጡላት ሌላ


63

ወረቀት ቢፅፉት እንደቃል አይሆንም
እንገናኝና ልንገርሽ ሁሉንም

ወሬ ምን ያደርጋል ነጋዴ እሚያመጣው
መገናኘት ነበር ናፍቆት የሚያወጣው

ወተቱን በሆዴ ቅቤውን በአንጀቴ
በራሰው በራሰው በራሰው አንጀቴ

ወተት በጨለማ ታበላሻላችሁ
ቀን እንዲህ ይገፋል እኔ ላሳያችሁ

ወታደር አይገባ አይበረብርብኝ
አንዲት ልጅ በሆዴ ባኖር ምን አለብኝ

ወዘፍዘፍ ያለ ነው የግራር አጥር
እኔ ለጅል ፍቅር እምብዛም አልጥር

ወይ ቶሎ ግደለኝ ወይ እድሌን ባርከው
ሊቀደድ ነው ሆዴ ሲርበኝ የማከው

ወይ አላሳጨድነው ወይ ከብት አልበላው
ከቶ መቼ ይሆን ያሳር የሚያልቀው?

ወይ አዲስ አበባ አገረ ገነት
የፊቱ ሲበላ የኋላው ሲሸት
የሚበላው ጮማ ማር ቅቤ ወተት
ቢመጡብሽ ምናል ቀንና ሌሊት

ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ
አቅፈው ያልሳሙት ሰው ይናፍቃል ወይ?

ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ
አገርም እንደ ሰው ይናፍቃል ወይ?

ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ
ዘንድሮም እንደ አምናው ሰው አለብሽ ወይ?

ወይ እድሌ ሃብቴ ምናባሽ ምናባሽ
እኔን ብቻ አይደለም አንቺም ግራ ገባሽ

ወይ እድሌ ሃብቴ የተልከሰከሰው
በሰባራ ምጣድ በገል የታመሰው

ወይ ካገሩ ውጭ ወይ ስምሽ ይለወጥ
እዚህ አገር ሆነሽ ሽተትሽኝ እንደወጥ
ካገሩም አልወጣ ስሜም አይለ ወጥ
እዚሁ አገር ሆኜ ልሽተትህ እንደ ወጥ

ወይ የአራዳ ልጆች ሽጉጥም የላቸው
በየደረሱበት ብርጭቆ ቦምባቸው

ወይ ድሬ ወይ ድሬ ወይ ማሩ ወይ ማሩ
እንኳን የሰው ልጅ አሸዋው ማማሩ

ወይፈኑ ቢታመም ጊደሯም ታመመች
ኧረ ለመሆኑ ያችስ ላም እንዴት ነች

ወደድኩሽ ውደጅኝ ይሸበር መንደሩ
ተኝቶ አለመያዝ ካለ ቁም ነገሩ

ወደ ጓሮ ዞሬ እንባየን ላንቆርቁር
ከነ መልኳ ጠፋኝ ቀይ ናት ወይ ጥቁር?

ወዲያ ወዲህ እያልኩ እኔ አልቀላውጥም
ስጋ በልቶ ጎመን ድሮውንም አይጥም

ወዳንቺ ስመጣ ሶስት ጊዜ ወደኩኝ
ይህ ለነፍሴ ቢሆን እንዴት በፀደኩኝ

ወዳጄ ነሽ እንጂ ጠላቴ ነሽ ወይ
የምትቀሰቅሽኝ ሌት እንደ ተባይ

ወዳጄ ዘመዴ ሲለኝ ከረመና
እርግፍ አርጎኝ ሄደ እንደ አሮጌ ቁና

ወዳጅ ለዘመዱ ቤት ይሰራ ቢሆን
ከሆዴ ዛፍ አለ ግድግዳ የሚሆን

ወዴት ሽርተት ሽርተት ያዳጠህ ይመስል
እኔ እንደ ብልሃቴ አረግሃለሁ ስል

ወዴት ትሄጃለሽ ሬሳ ዘርግተሽ
ታምሜ ታምሜ ሲጠናብኝ ይተሽ
እኔን ማጣጠቡን መገነዙን ትተሽ

ወድጄሽ ወድጄሽ መጣላት ሲመጣ
አንደዜ ኩፍኝ ነኝ አንደዜ ፈንጣጣ

ወድጄሽ ወደሽኝ ዝናው ካልተሰማ
ውሻም ሊጥ ይደፋል አንዳንድ ቀንማ

ወገን ለወገኑ ቤት ይሰራ ቢሆን
አጥንቴ ግድግዳ ጎኔ ማገር ይሁን

ወጣሁ ወጣሁና ቀረሁ ከዳገቱ
ሬሳሽን አንሺ በሏት ያቺን ገልቱ

ወፊቱ ብር በይ እያት ያቺን ደሃ
እንባየን አጠጫት ጠምቷት እንደሁ ውሃ

ወፊቱ ብር በይ ጠይቀሻት ነይ
እኔ አጣሁ አምሳያ እሷ አገኘች ወይ?

ወፊቱን ገድላችሁ ክንፏን ስደዱልኝ
ስበር እኖራለሁ መቼም አላለልኝ

ውሸቴን ነው እንጂ እህህ ማለቴ
እንዳይወጣ አውቃለሁ ቤቱ ነው አንጀቴ

ዋ ብየ ልለይሽ ዘመድ እንዳረዱት
ሰቀቀን ነውና የሩቅ ሰው ቢወዱት

ዋና አውቃለሁ ብየ ገብቼ ባህር
ምን ትበል እናቴ ቀልጨ ስቀር

ውሰጂው ውሰጂው ከጭኔ ፈልቅቀሽ
የቀማኛ አገር ነው ሳንቺም ተጠንቅቀሽ

ውሻ ነህ ውሻ ነህ የራስ ቅቤ በላ
ወዴት አደረስከው ያንን ሁሉ ማላ?

## ዘ

ዘመቻ ታዘዘ ይኸው መሄዴ ነው
አደራ እሚባለው ምን አይነቱ ሰው ነው?

ዘንድሮስ አምላኬ እንዴት ጉድ ሰራኝ
ሳልለምነው ሰጥቶ ሳልጠግባት ነሳኝ

ዛፍ ተንተርሶ ነው ዝሆን ሲያንቀላፋ
በህልሜ እንዳላይህ ከነእንቅልፌ ጠፋ

ዛፍ ያጣ ጉሬዛ አዳኝ ያበረረው
የማትሆነኝ እንደሁ ልቤን ተው ልበለው

ዝናቡ ዘነበ አትውጭ ስልሽ
ያው እንደፈራሁት ጎርፉ ወሰደሽ

ዝናቡ ዘነበ ደጁ ረሰረሰ
ቤት ያላችሁ ግቡ የኛስ ቤት ፈረሰ

ዝናቡ ጣለ አሉ ጋራ ጋራውን
ጎርፍ ያመጣሽ እንደሁ ልጠብቅ ወንዙን

ዝናብ ዘንቦ ዘንቦ ሲያባራ ያካፋል
ጠይም የወደደ ሲሄድ ያንቀላፋል

ዝንጀሮ ከገደል ወድቆ አይሰበርም
እንዝርት አለቋንጣ አይሽከረከርም
ይዘገያል እንጂ ያሰብነው አይቀርም

ዞሮ በዲሞትፈር ካለአንጎራደደው
እኔ እናቱ ነኝ ወይ ሲሸሽ የምወደው

## የ

የሄድክበት መንገድ አቧራውን ቅሜ
የአረፍሽበት ጥላ ግንዱን ተሳልሜ
ሞትኩልሽ አንቺ ልጅ በአንድ ቀን ታምሜ

*የሆዴን በሆዴ የአፌን በእንጉርጉሮ*
*እንዳልናገረው ቀኔ አይደል ዘን-ድሮ*

*የሆዴን መቃጠል ጥርሴ እየመለሰው*
*አሁን በጎ አዳሪ እመስላለሁ ለሰው*

*የለህም አይባል ይመሻል ይነጋል*
*አለህ እንዳይባል እንዲህ ይደረጋል*

*የልቤን በሆዴ እስኪ ላመላልሰው*
*እንዴት በመፋቂያ በጥርስ ይሞታል ሰው*

*የማላውቃትን ልጅ ማን አስገቡ አላችሁ*
*እሷም ታይታ ጠፋች እኔም ሞትኩላችሁ*

*የማትመጣ እንደሆን የምትቀር በዛው*
*ል-ብላ ምናምኑን ኩራቴን ልተው*

*የሚበላ ሞልቶ ሳይጠፋ ከአገሩ*
*አንጀት ትበላለች ምንድን ነው ምስጢሩ?*

*የሚወዱትማ ስንት ቀን ይገኛል*
*አመለኛው ጎኔ ከማንም ይተኛል*

*የማገኝሽ ቢሆን ገብርኤልን ባዘከርኩ*
*የማገኝሽ ቢሆን ማርያምን ባዘከርኩ*
*እንኳን ለጨዋታ ለአይኔም ተከለከልኩ*

የምትበሉም ብሉ የምትጠጡም ጠጡ
እኔ በምወዳት በዛች ልጅ አትምጡ

*የሰውን እንጃ እንጂ እኔስ በበኩሌ*
*በነበረው መፅናት ይወዳል አመሌ*

*የሰው የለው ሞኝ የሰው የለው ሞኝ*
*ከአገሩ ከቦታው ከስፍራው ሲገኝ*

*የስምቡል ሙቀጫ የወይንዛረግ ጠጅ*
*የወደደ አይሞትም ይታመማል እንጂ*

የቀበናን መንገድ አየሁት በህልሜ
እንዴ እግሬ ይግባ እንጂ አልወጣም ደግሜ

የቀበናን ውሃ ቀዳነው በወንፊት
እኔ ነኝ ወይ አንቺ የከዳነው በፊት

የቆለኛ ፍቅር ሲይዙት ማማሩ
ቅልጥ ይላል እንጂ ጣይ ሲሆን አገሩ



የቆንጆች መዲና የተባለልሽ
እንዳው በጥቅሉ ወሎ እንደምንነሽ

የበረሃ አሞራ አዳኝ ያበረረው
የማትሆኝኝ እንደሁ ልቤን ተው ልበለው

የበረሃ አሸዋ ንፋስ የገነባው
እንግዲህ መሸለት ልቤን ግራ ገባው

የበረቱትማ እያዩሽ አለፉ
ሳይሽ የምደክመው እኔ ነኝ ሰነፉ

የበደልሽኝ በደል መቼ ያለማምዳል
እንደው እንዴት አደርሽ እንዴት ዋልሽ ይበቃል

የባህር ዳር ጨፌ ያበቅላል ጠንበለል
ዋጥ ላርግሽና አላየሁም ልበል

የባቡሩ መንገድ ወጋው ተረከዜን
ሰው ሁሉ አወቀብኝ ባንቺ መተከዜን

የባቄላ ጠላ የጤፍ አሹቅ የለው
ምንም ቢዋደዱ የባዳ ውል የለው

የቤት እቃ ገዛሁ ሰፌድ እንቅቡን
ይኸ ጓዳ ስንቱን ይችለው ይሆን

የተንቀለቀለች እንደ እንጦጦ ንፋስ
እኔም ሰው ነኝ ብየ መከተሌ ይባስ

የተኛሽበትን ሳታመላክችኝ
ስታዞሪኝ አደርሽ ስታንከራትቺኝ

የታማሁት እኔ ነገር የበዛብኝ
አንች ምን አግኝቶሽ ከሳሽ ጠቆርሽብኝ?

የት አባክ ምን አባክ የእንቅብ አዛይ ልጅ
እተካብሃለሁ ደህና ልሁን እንጅ

የአለሽበት አገር ስፍራው ራቀና
በላሁ ምናምኑን ርሃቤ ጠናና

የአመኝ የነበረ እያለሳለሰ
ሰው መውደዴን ብተው ገላየ መለሰ

የአምባሰል ማር ቆራጭ ይወጣል በገመድ
ወደ አንቺ እሚያመጣኝ ወይ ዘመድ ወይ ዘመድ

የአምባሰልም ዳገት የእድገቴ ስፍራ ነው
የጦሳም አቀበት የቆረብኩበት ነው
ዛሬስ በቀላሉ ከአፋፍ ጣለኝ ምነው?

የአምባሰል ተሟጋች ሲሄድ አጎንብሶ
ሲመለስ ቀና አለ የልቡን አድርሶ

የአምባሰል ተሟጋች አያውቅም ይግባኝ
በበሽታየ ላይ አንቺን ጣለብኝ

የአምናን ቀን አማሁት ለአፌ ለከት የለው
የዘንድሮው መጣ እጅ እግር የሌለው

የአረሰም ዘራና የዘራም አጨደ
የአጨደም ከመረ የከመረም ወቃ
የወቃም አስገባ የአስገባም አስፈጨ
የአስፈጨም ጋገረ የጋገረም በላ
የእኔና አንቺ ፍቅር ቀረ እንደተጉላላ

የአራት ኪሎ ልጆች እነ ድንጋይ ኳሱ
ምን ጊዜ ተጩሆ ምን ጊዜ ደረሱ

የአራት ኪሎ ልጆች ጥርሰ ነጫጮቹ
ለፍቅር ነው እንጂ ለጠብ አይመቹ

የአራዳ ልጅና የሻሸ መቀነት
ሲያጠብቁት አይወድም ሸብ እንደ ዘበት

የአሳ ሽማግሌ አቀበት ይዋኛል
አትሸበር ሆዴ የበለጥ ይገኛል



የአሳብና የጅብ ለሊት ነው ጉልበቱ
ቀንማ ምን ይላል ከሰው ሲጫወቱ

የአሳደከው ፈረስ የአመንከው ሰው ይክዳህ
እኔማ ድሃ ነኝ በአዝን ምን ልጎዳህ

የአቀመሸኝ ቅጠል ምንድን ነው ማርከሻው
ሰው ጠልቼ ቀረሁ እስከ መጨረሻው

የአባት አገር ጋቢ የእናት አገር ሽማ
ነጠላ አይደለም ወይ የሰው አገርማ

የአባት እዳ ለልጅ ይባል ነበር ድሮ
በአያት እዳ ገባሁ እኔማ ዘንድሮ

የአባይ ውሃ ሞልቶ ይሄዳል ቦይ ለቦይ
ምነው በልሜ መጣሽ ደህና አይደለሽም ወይ?

የአባይ ጥቁር እንጨት ባህር ያጠለቀው
መች እወድህ ነበር መለየቴን ባውቀው

የአንቀጥቅጥ አለብኝ የአንሰፍሰፍ አለብኝ
የምወዳትን ልጅ ሌላ ሲነካብኝ

የአንቺስ ቆረጠልሽ ስለት ነው መሰለኝ
እየገዘገዘ የኔስ ሆድ እምቢ አለኝ

የአንቺን አመጡና ለኔ ነገሩና
የኔን ወሰዱና ለአንቺ ነገሩና
ተደላድለው ተኙ አለያዩንና

የአንቺ አንጀት ይሻላል መቀነት የያዘው
የኔ አንጀት እምቢ አለ በአሰረው ብገንዘው

የአዳል ቤት ሲቃጠል አይታይም ጭሱ
የማትቀር ልጅ ቀረች እስኪ እጣን አጭሱ

የአዳጠሽን ጠጠር ስለቅም ሳስለቅም
ደሞ ወደቅሽ አሉ የአንቺ ጉድ አያልቅም

የአዳፈኑት እሳት ለነገ ያሉት
አያሳዝንም ወይ ጠፍቶ ሲያገኙት

የአገራችን ታቦት ዝክረ ብዙ ነው
ከኔ ወዲያ ድሃሽ ለማኝሽ ማነው

የአገሬ ልጅ ብትሆን ይህን አትሰራኝም
የወንዜ ልጅ ብትሆን ይህን አትሰራኝም
የሰው አገር ሰው ነች ትቅር ግድ የለኝም

የአገሬ ልጅ ነሽ ወይ በዛ የዘለቅሽ
ተጣልቼሽ ነበር እስኪ ልታረቅሽ

የአገሬ ልጅ ናና የወንዜ ልጅ ናና
በአዘን በመከራ አንለይምና

የአገሬን ልጅ ትቼ የሰው አገር ሳድን
የወንዜን ልጅ ትቼ የሰው አገር ሳድን
ቀረሁ እንደ ካሳሁ ጎኔ ሳይደነድን

የአገር ልጅ በገንዘብ ይለወጣል ወይ
ሲሞቱ እሚቀብር ሲታመሙ እሚያይ

የአጣም ያገኝና ያገኘም ያጣና
አንተ የምትይኝ አንቱ ትይኝና
ያስተዛዝበናል ይኸ ቀን ያልፍና

የእባብ ሽማግሌ አቀበት ይዋኛል
አትሽበር ሆዴ የበለጥ ይገኛል

የእኔ በሽታየ ድርብ አይወድልኝ
እባክሽ አንቺ ልጅ ባልሽን ፍቺልኝ

የከፋው ሰው ሲሄድ ስንቅ አይል ስልቻ
ጊዜ እንኳን የለውም የመሰናበቻ

የከፋው ሰው ሲሄድ አይሰጡ ስንቁን
እየበላው ይሂድ አንጀት አንጀቱን

የኩባያ ወተት የለውም አረፋ
በሽታየን የሚውቅ አስታማሚ ጠፋ

የወሎ ልጅና የጣት ወርቅ አንድ ነው
ሹልክ ያለ እንደሆነን ፈላጊው ብዙ ነው

የወሎ ሰው ማለት ምንድነው ቅመሙ
የሚያስደነግጠው ገና ሲወጥኑ

የወደዱትማ ስንት ቀን ይገኛል
አመለኛው ጎኔ ከማንም ይተኛል

የዘንድሮ ነገር የተገላቢጦሽ
አህያ ወደ አጥንት ውሻ ወደ ግጦሽ

የዛች ልጅ እናት ውጪ ተከሰሻል
እንዲህ ያለች ቆንጆ ማን ውለጅ ብሎሻል

የዛችን ልጅ መንገድ እጠሩት በኮባ
አመለኛው ልቤ ገደል እንዳይገባ

የደገኛ ፈረስ አይበላም ገለባ
የኔ ልብ ምኝ ነው አለቦታው ገባ

የጎረቤት ወዳጅ እንዴት ደግ ነው
እንቅቡም ሰፌዱም ተላላኪ ነው

የጎረቤት ወዳጅ ይቅር ብየ ብተው
አይኔ መሰከረ ቅሌት አይታክተው

የጎበዝን ወዳጅ ጎበዝ አይደፍራትም
የመንደር አውደልዳይ ቢያገኝ አይለቃትም

የጎጃም ነጭ ጤፍ የጌቶቹ ምሳ
የት አገኝሻለሁ ብቀመጥ ብነሳ

የጎጃም አገልግል ሃር ነው ሰበዙ
እቱ ባንቺ ነገር ሰማሁ ብዙ ብዙ

የጠይም አይናማ አስቀምጨ ቤቴ
በላሁ ምናምኑን ቢታጠፍ አንጀቴ

የጠዳ መኝታ ሁልጊዜ ተለሙዶ
ያ የታጣ ለታ ነጋ ጠባ መርዶ

የጤፍ መሰለቂያ ይላል እሽም እሽም
እመጣለሁ ብሎ ቀንጆ ልጅ አይዋሽም

የጦሳን አቀበት ወጣሁት ተክዤ
በእጄ ምናምኑን በልቤ አንቺን ይዤ

የጦሳን አቀበት ዝንጀሮ አይወጣውም
ሰው ከተዋደደ እንከን አያጣውም

የጨለማው ዘመን ክረምቱም አለፈ
ልቤ ብቻ ቀረ እንደተነደፈ

የጨረቃ ፈታይ የኮከብ አጠንጣኝ
ህልም አላየህም ወይ ወደ አንተ እሚያመጣኝ

የፈረንሳይ ባቡር ቢሄድ አይታክተው
እስኪ መድረሻሽን ቆሜ ልመልከተው

የፈረንሳይ ቋንቋ የማልችለውን
ውይ ውይ አሰኘችኝ ሴቷ ልጅ ወንዱን

የፍቅር መረዋ ሲደወል ሰምቼ
ሃሙስ ጎንደር ገባሁ ሮብ ተነስቼ

የፍቅርን ነገር ያየ ሰው ይፍረደኝ
እዩት እንደ አንበጣ የጎድን ሲያስኬደኝ

ያም አለ ያም አለ የአተር ገለባ ነው
ሳቅና ጨዋታ ከነቆንጂት ጋር ነው

ያቺን ማዶ ጋራ ስሟን ማን ይሏታል
አላፊው አግዳሚው አፋፏን ያያታል

ያቺን ማዶ ጋራ እንደምን ልውጣት
እኔስ ደስ የሚለኝ አፋፏን ሳያት

ያንን ማዶ ጋራ ተራራ ጋርዶታል
እሱ እንደኔ እንደሆን አይድንም ይሞታል

ያው ዘመድ ያው ዘመድ ያው ዘመድ ይሻላል
ባዳ ተሰቦ ነው ቀን አይቶ ይጥላል

ያዳፈኑት እሳት ለነገ ያሉት
አያሳዝንም ወይ ጠፍቶ ሲያገኙት

ያገናኘን እንጂ ክፉ ደጉን አይተን
እንዳንቀር አውቃለሁ እንዲህ ተለያይተን

ያ ጥቁር አሞራ ግንባረ ቦቃው
ዋ ብሎ መለየት ማን አስተማረው

ይሂዱ ይሂዱ ይሂዱ ብለናል
እኛም በጊዜያችን በሰው ላይ ሄደናል

ይመራል ይላሉ ኮሶ መጠጣት
ከእሱስ የሚመረው ወዶ መለየት

ይመጣ እንደሆነ ያገሬ ልጅ ይምጣ
በአንድ ቀን ጨዋታ ናፍቆት የሚያወጣ

ይሻለኛል ብየ ቀይ በቅሎ ብገዛ
እሷም ሰጋር ሆነች ተፈንጣጪም በዛ

ይሻላታል ብየ ገዳም ብልካት
ከቶ አልተሻላትም አባባሱባት

ይበለኝ ይበለኝ ይበለኝ በጣም
እንዲህ ካላረጉት እብድ አይቀጣም

ይበልጥ አገኝ ብለሽ ስትይ ወጣ ወጣ
የእጅሽን አገኘሽ አቤት የአምላክ ቁጣ

ይቺንስ ጎጆየን አቃጥላታለሁ
ሲያጤሱ እየጤሰች ያለኝ እመስላለሁ

ይኸው ምልክቱ ከደብዳቤው ላይ
ቀለሙን ያጠፋው እንባ አይደለም ወይ?

ይኸ ፍቅር ማለት ሞኝ ነው ጨርሶ
እሞታለሁ ይላል በሰው ገንዘብ ደርሶ

ይኸ ፍቅር ማለት እንደምን አይነት ነው
እኔስ ያየሁቱ እጅ እግርም የለው

ይወዘውዘኛል እንደ ሃረግ ዛፍ
ያለቀኔ ሳልሞት ከቀኔም ለአሳልፍ

ይገብር ካላችሁ ዝንጀሮም ይገብር
የንጉስ አይደለም ወይ የሚጭረው ምድር

## ደ

ደህና እደሪ ቢለኝ አልኩት ደህና እደር
እንደ ሴቶቹ አመል እንደ መግደርደር
ያአልጋ ደፉን ይዞ ቆሞ ለማደር

ደረቴን በጥይት ሽንጤን በጎራዴ
አገጨን በቡጢ ሳንጃውን በሆዴ
ራሴን በዱላ ደም በደም ሳላይ
ያቺን ልጅ በዋዛ መልቀቅ አለ ወይ

ደርባባ ደርባባ ይወልዳሉ እናቷ
እሷም ደርባባ ነች ትበልጣለች እቷ

ደሴ ምሳ በልተን ቦሩ የቀነኛ
መኪናው ዘለቀ መጣች ያች ጠንቀኛ

ደሴ አድራለሁ ብየ ኮምቦልቻ መሸብኝ
እተወዋለሁ ስል ደሞ አገረሸብኝ

ደሴ ግራር እንጂ አያበቅልም ጥድ
ፍቅር ስመጨረስ ያልታደልኩ ጉድ

ደሴ ጥንቅሽ በልቶ አበደ ሰውየው
ኮምቦልቻ ቆንጆ አይቶ ጉድ አለ ሰውየው
መች እለቀዋለሁ የጁን ሳላሳየው

ደስ ያለው ደስ ብሎት የከፋው ከፍቶታል
ይኸን ጊዜ ቤቴን በርባሪ ገብቶታል

ደብዳቤ ቢፅፉት እንደ ቃል አይሆንም
እንገናኝና ልንገርሽ ሁሉንም

ድሃ የድሃ ልጅ መሰረተ ድሃ
ስጋ በልቶ ጎመን ጠጅ ጠጥቶ ውሃ

ድሮም ስትፈጠር ጠማማ ነበረች
አርብ ሞተችና ሃሙስ ተቀበረች

ድንጋይ ብወረውር ደረቱን መታሁት
አወይ ኩላሊቱን ልቡን ባገኘሁት

ዶሮ ውሃ ጠምቶት አንጋጦ ይጠጣል
መለየት ክፉ ነው መረሳት ያመጣል

ጀ

ጀመረ ባላገር ነገር ያላምጣል
አበጀሁ በላኋት ቢሉት ምን ያመጣል?

ጀንበሪቱ ገባች ጨረቃ ተክታ
ያለሰው ቢወዱት ምን ያደርጋል ቦታ



77

ጀግና ብርሴ ነው ቶሎ ይሰበራል
ፈሪ ነው ተራራ ዝንት አለም ይኖራል

ጅብ በለሊት ሲሄድ ያደርጋል ጉርድምድም
እንዴት ነው ላይ ደሴ ፈረንጅ አምባ ግድም

## ገ

ገራዶ ሞላ አሉ እቀጤማው ድረስ
ሰው ናፋቂው ልቤ ሄደ ላይመለስ

ገራዶ ሞላ አሉ እቀጤማው ድረስ
ሲወዱ ነው እንጂ ከጠሉ አለመድረስ

ገበያ አመለጠኝ ጧት የተስማማሁት
ይህን ድህነቴን ማጣቴን ጠላሁት

ገና ዛሬ አየሁት በሽታየን በልሜ
ለካ አንቺ ኖረሻል ህመሜ ድካሜ

ገዳም ገባሽ አሉ ደብረ ሊባኖስ
ሰው እየገደሉ ይማራል ወይ ነፍስ

ጉም እጅ እግር የለው ይወጣል ተራራ
ሰውነቴ ከዚህ ልቤ ካንች ጋራ

ጉም እጅ እግር የለው ይወጣል ከሰማይ
ልቤን ሰረቀችው ሳልሰማና ሳላይ

ግርም ያረገኛል ያሰብኩት እንደሆን
ሰው በገዛ አገሩ ስደተኛ መሆን

ግቢ ተቀመጭ ራቁቴን ነኝ
ከአንቺ የተለየ ምን አካል አለኝ

ግባና ላሳይህ እርቅናየን ቆሜ
ምን አከላት አለኝ ከአንተ የተለየ

ግዜ ያመጣውን ግዜ እስኪመልሰው
አሰሱም ገሰሱም ተጫወተ በሰው

ጎበዝና ፈሪ ሁለት መልክ ይዘህ
ጥርስህ ሰው ገደለ ሲሸሽ ከንፈርህ

ጎንደር አባ ጨሌ ውስጡ ጨለማ ነው
እሷንም አባክናት እኔን ብቻ ምነው

ጎጃምና ጎንደር ማዶ ለማዶ ነው
ፍቅር አለቦታው አባ ጨጓሬ ነው



## ጠ

ጠይም ልጅ አርግዛ ጠንቶባታል ምጡ
እሷም እህ ትላለች እናንተም አዳምጡ

ጠይም ተፈትፍቶ ሲበላ ደርሼ
መከራየን አየሁ ሲያቀብጠኝ ቀምሼ

ጠይም ወዶ ወዶ በቀይ ሲመለሱ
አዙሮ ይደፋል ጠጅ እንደ ቀመሱ

ጠይም ዘለግ ያለ ጎራዴ ታጣቂ
ሲቀመጥ አሳዛኝ ሲሄድ ተናፋቂ

ጠጅማ ብጠጣ አሁን ማን ችሎኝ
ጮማማ ብበላ አሁን ማን ችሎኝ
ቀለቤ ገብስ ሆኖ በሶ አደከመኝ

ጠጅ እንደጠጣ ሰው በውሃ ሰክሬ
ልጁን አኮራሁት የልቤን ነግሬ

ጠጋ ብለሽ ተኝ ወደ ግድግዳው
ከልቤ ላይ ብትሞች የማነው እዳው?

ጣል ጣል አርጉብት እስኪ ከነገሩ
እንዲከፋኝና እንድሄድ ከአገሩ

ጤና ይስጥልኝ ባልል ባይናገር አፌ
ደጅ መጥናቴ እኮ ነው በደጅሽ ማለፌ

ጥፍርህ ዘረዘረ አደገብህ በጣም
ቆርጨልሃለሁ እንግዲህ አልመጣም

### ጨ

ጨረቃ ባይወጣ ሰው ባይነጋገር
ያቺ ልጅ በጥርሷ ገድላን ሄዳ ነበር

ጨዋታው ጥሩ ነው እስከ ጊዜው ድረስ
ሲያፈቅሩ ነው እንጂ ከጠሉ አለመድረስ

ጮማና ፍርንባ ሞልቶላት በአገር
አንጀት ትበላለች የድሃ ነገር

### ፈ

ፊርማና ወረቀት ጠፊ ነው ተቀዳጅ
መተማመን ብቻ ይበቃል ለወዳጅ

ፊትማ ጥንትማ ድሮማ ተበልቶ
ከጠላው ከጠጁ ከብርዙም ተቀድቶ
ከጠላው ከጠጁ ይጠጣ ነበረ
ዛሬ መበተኛው ነገር ሆኖ ቀረ

ፋኖ አገሩ ገባ ሳይሰናበተኝ
እሸኘው ነበረ ምንም ቢታክተኝ

ፋጢማም አገባች ከድጃም ታጨች
እንግዲህ ላይ ደሴ ምን አገር ሆነች

ፍርድ ቤት እንድሄጂ እቃ ቢጠፋሽ
እዛው ከጎረቤት እኔው ነኝ ሌባሽ

ፍቅሬ የአገሬ ልጅ ምን ልሁንልሽ
ስራየም መንገዴም ሆነ በደጅሽ

ፍቅር ሰው ገደለ ሲሉም አልሰማሁ
ያከሳል ያጠቁራል ቀምሸዋለሁ


80

ፍቅር በአገር ግዛት በቀላጤ ነው ወይ
የምትሆነኝን ሰው እኔ አውቃት የለም ወይ

ፍቅር በዛ ፀሃይ እንዳብከነከነኝ
መሰንበት ደግ ነው ለጥል አደረሰኝ

ፍቅር አይዘኝም እያልኩ ስመካ
ይጋግረኝ ጀመር በአብሲት እያቦካ

ፍቅር ይብላኝልህ እኔ አንተን አያርገኝ
እኔ እንግዲህ አልቀል ካልቀለሉ አትገኝ



## በአማርኛ ዘቀን ግጥሞች (በዋሸራ ፎንት የተመታ)

አረሱት መተማን ዘቅዝቀው እንደ ቦይ
አረሱት አርማጭን ዘቅዝቀው እንደ ቦይ
አረሱት ቋራንም ዘቅዝቀው እንደ ቦይ
አባትየው ቢሞት ልጅየው የለም ወይ?
(ጎንደር አዝማሪ ቤት የተሰማ ግጥም 'ፍትህ' ጋዜጣ ጥር 2003)

እንዲህ አርገን ስራውን ሁሉ አምነን
እናምናለን ዳግም ይመጣል ብለን
ነገር ግን ዳግም ይመጣል ስላልን

*ከፃድቃንም ከመለአክትም ቢሆን*
*የሚያውቅ የለም የሚመጣበትን ቀኑን*
*ባላወቅነው ባልጠረጠርነው ሰአት*
*ግሩም ሆኖ ይመጣል እንጂ ድንገት*
*መጀመሪያ አዋጅ ነጋሪት ሲመታ*
*ከያለበትት ይሰበሰባል አንዳፍታ*
*አጥንታችን ትቢያ የሆነው አፈር*
*ጅብ የበላው የተበተነው ከዱር*
*የራስ ጠጉር የእግር ጥፍራችን ሳይቀር*
*ተሳስቶ አንዱ ወደ አንዱ ሳይዞር*
*በየራሱ ይሰበሰባል ሁሉም*
*ይመታና ያዋጅ ነጋሪት ዳግም*
*ነፍስ የሌለው በድን ይሆናል ፍፁም*
*በሶስተኛው ያዋጅ ነጋሪት ሲመታ*
*ይነሳሉ መልካም የሰሩ በእልልታ*
*......የብርሃን ቀሚስ ለብሰው*
*እንደፀሃይ እንደ ጨረቃ ደምቀው*
*እግዜአብሄርን ፈጣሪያቸውን መስለው*
*ይሰሙና በቀኙ ቆመው ፍርዱን*
*ከማያልቀው ከተድላ ደስታ በቀር*
*ጠግቦ ቁንጣን ተርቦ ስስት ሳይኖር*
*ገብቶ መውጣት አግኝቶ ማጣት ችግር*
*የሌለባት ደገኛይቱን አገር*
*ይወርሳሉ መልካም የሰሩ በምድር*
*ሀጥአንም እጅግ ከጭራ ቀጥነው*
*መልካቸውም እጅግ ከቁራ ጠቁረው*
*ከላይ እታች የጨለማ ልብስ ለብሰው*
*ዲያቢሎስን አለቃቸውን መስለው*
*ይሰሙና በግራ በኩል ቆመው*
*በመንቀጥቀጥ የሚፈርደውን ሰምተው*
*ከልቅሶና ጥርስ ማፋጨት በቀር*
*ተድላ ደስታ የሌለባትን አገር*
*ይወርሳሉ ክፉ የሰሩ በምድር*
*እንዲህ አርጎ መፃህፍት ሁሉ እንዳሉ*
*ይከፍለዋል እንደስራው ለሁሉ*